# በጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶች እና የዘመን መንፈስ፤ በአዲስ አበባ፤ ጃን ሜዳ (ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም)

# Major Events in Epiphany Ritual and Zeitgeist, at *Jan Meda* in Addis Ababa (from 1925-1974)


**ሰሎሞን ተሾመ[1]**

**Solomon Teshome**



## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ የጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶች በማሳየት በወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ጃን ሜዳ በሚባለው ስፍራ ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ባሉት አመታት የተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶችን በቅደም ተከተል በማቅረብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ስልትን የተከተለ ሲሆን፣ በቃላዊ ታሪክ የፎክሎር ጥናት ዘርፍ የሚመደብ ነው፡፡ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ለቀዳማይ መረጃዎች ቃለመጠይቅና ንጥል ሁነት ማሳያ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን፣ ከተለያዩ መዛግብት የተገኙ ካልዓይ መረጃዎችም ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያላቸውን ትርጉምና በወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ ለመመርመር ‘‘ኦራላይዝድ ሂስትሪ’’ የንድፈሃሳብ መንገድን የተከተለ ነው፡፡ በእነዚህ ዓመታት በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ወቅት ንጉሱ፣ መኳንንት፣ መሳፍንት፣ የኃይማት አባቶች በስፍራው በመገኘት የተለያዩ መንፈሳዊና ዓለማዊ ስርዓቶችን ይፈጽሙ እንደነበር ጥናቱ ያሳያል፡፡ የጥምቀት በዓልም ከኃይማኖታዊ ስርዓትነቱ በተጨማሪ የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ማከናወኛ ሕዝባዊ መድረክ በመሆንም ያገለግል እንደነበር ጥናቱ ያሳያል፡፡ በጃን ሜዳ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ ከተለያዩ አለማት የመጡ የኃይማኖት አባቶች፣ ዲፕሎማቶች፣ አምባሳደሮችና የሀገራት መሪዎች ይገኙ ነበር፡፡ ይህም የጥምቀት በዓል ለዲፕሎማሲ፣ ለሕዝብ ለሕዝብ ትስስርና ለሀገር ገጽታ ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ጥናቱ ያሳያል፡፡ ሀገሪቱ ውስጥ የተከሰቱ አበይት ታሪካዊ ሁነቶች በጥምቀት በዓል አከባበር ላይ የፈጠሩት ተጽዕኖ እንዲሁም የዘመኑን መንፈስ እንደሚያሳዩ ጥናቱ አመላክቷል፡፡



**ቁልፍ ቃላት**:- የጥምቀት በዓል፣ ቃላዊ ታሪክ፣ የዘመን መንፈስ፣ ‘‘ኦራላይዝድ ሂስትሪ’’



## Abstract

This study aims to analyze the zeitgeist in the epiphany ritual, focusing on major events that happened from 1925 to 1974. Specifically, the study examines the Epiphany ritual held at *Jan Meda* in Addis Ababa and the major events during those years, presenting these events chronologically. The



[1]የፎክሎር ጥናት ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር፣ ባሕርዳር ዩኒቨርስቲ፡- solomontesh12@gmail.com

research adopts a qualitative methodology from a folklore studies perspective, utilizing an oral history approach. In the study, primary and secondary data were collected and used. Primary data were collected using interviews and case study data-gathering techniques, while secondary data were gathered from archival sources. The data were analyzed qualitatively. In analyzing and interpreting the zeitgeist within the temporal time, “Oralized History” was used as a conceptual framework. The findings reveal that, during the specified period, the Epiphany rituals were significant as religious events and sociopolitical and cultural platforms. In the Epiphany rituals, major events, which are religious and secular, happened with the attendance of Emperor Haile Selassie, members of the nobility, judicial authorities, and spiritual leaders. The Epiphany ritual was used as a major venue for diplomatic engagement, fostering people-to-people connections and contributing to nation-building. This is also evidenced by the attendance of spiritual leaders, diplomats, ambassadors, and heads of state from diverse nations at the Jan Meda rituals. Finally, the study underscores the reciprocal relationship between historical events and the ritual of the Epiphany, demonstrating how the sociopolitical dynamics of the time influenced the ritual's practices and how, in turn, these practices reflected and shaped the spirit of the time.

**Keywords:** Epiphany Rituals, Oral History, Zeitgeist, Oralized History, *Jan Meda*

## 1. የጥናቱ ዳራ

ጥምቀት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያየ ትርጓሜዎች አሉት፡፡ ከእነዚህ ትርጓሜዎች መካከል በውኃ መንጻትን፣ በመንፈስ ቅዱስ መጎብኘትን፣ መሞትን እንዲሁም በስቃይ መጠመቅን የሚያሳይ ነው (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ 1992 ዓ.ም)፡፡ ከትርጓሜዎቹ መካከል አንዱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ ከወንዝ የተጠመቀው ጥምቀት የውኃና የመንፈስ ጥምቀት ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ጥምቀት የሚለው ቃል የ‟ኢየሱስ ክርስቶስን በውኃ መጠመቅ” የሚለውን ትርጉም የያዘ ነው፡፡

ክርስቶስ በሰላሳ አመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ መጠመቁን መታሰቢያ በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥር 11 ቀን የጥምቀት በዓልን በየአመቱ በደማቅ ስርዓት እንደምታከብር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (1994 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡

በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት አስተምህሮ ዓበይት የአደባባይ በዓላት መካከል አንዱ የጥምቀት በዓል ነው፡፡ የጥምቀት በዓል በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች በየአመቱ በድምቀት ይከበራል፡፡ በዓሉ

ከሚከበርባቸው ቦታዎች መካከል ጃን ሜዳ አንዱ ነው። ጃን ሜዳ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ሕዝባዊ ቦታዎች (puplic places) መካከል አንዱ መሆኑን ሰሎሞን (2007 ዓ.ም) ይገልጻሉ።

ጃን ሜዳ የሚለው ቃል ትርጓሜን በሚመለከት ደስታ (1962 ዓ.ም፤399-400) "ጃን ሜዳ (ሜዳ ጃን) የንጉሥ ሜዳ ንጉሡ የጦር ሰራዊት ሰልፍ የሚያይበት ከባሎሚሎቹ ጋር ጉግስ የሚጫወትበት ሜዳ፣ በጎንደርና በአዲስ አበባ ይገኛል።" በማለት ይገልጻሉ። በተመሳሳይም ሥርግው (1983 ዓ.ም፤431) "ጃን ሜዳ፣ የጃን ሆይ ሜዳ ወይም የንጉስ ሜዳ ማለት ነው።" በማለት ይገልጻሉ። ስፍራውን ጃን ሜዳ ብለው የሰየሙት አጼ ምኒልክ ሲሆኑ፣ ስፍራው ለሕዝብ መሰብሰቢያ፣ መዝናኛና የስፖርት ማዘውተሪያ እንዲሆን ታስቦ የጠዘጋጀ ሲሆን፣ ወደ 800,000 ሜትር ካሬ ስፋት ያለው ነው (ሥርግው፣ 1983 ዓ.ም)።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ጃን ሜዳ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ባሉት አመታት የተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶችን በቅደም ተከተል በማቅረብ በየወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ መመርመር ነው። የጥናቱ ወሰን ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ባሉት አመታት የሆነበት ምክንያት የጥምቀት በዓላት እንዴትና በምን ሁኔታ ይከበሩ እንደነበር የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ ያገኘሁት በ1917 ዓ.ም መታተም በጀመረው "ብርሃንና ሰላም" ጋዜጣ ላይ ነው። ከዚህ ጋዜጣ በፊት በጥምቀት በዓል የአከባበር ስርዓት ላይ በጽሑፍ የቀረበ መረጃ ማግኘት ባለመቻሌ የጥናቱን መነሻ ከ1917 ጀምሮ ባሉት ሀምሳ አመታት ለመወሰን ተገድጃለሁ። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ እስከ 1966 ዓ.ም የተወሰነው በዚህ ዓመት የተደረገው የመንግስት ለውጥን መነሻ በማድረግ ነው።

በጥምቀት በዓል ላይ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበዋል። ከእነዚህ መካከል "የጥምቀት በዓል ምንነቱ፣ ማሕበረ-ባህላዊ አውዶቹና ፋይዳዎቹ" በሚል ርዕስ አበባው ይርጋ (2006) በ"ኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት" ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል። በጥናቱም የጥምቀት በዓል ምንነት፣ የአከባበር ሂደትና ያለው ማሕበረ-ባህላዊ ፋይዳ ምን እንደሚመስል ተመላክቷል።

"የጥምቀት በዓል የአከባበር ስርዓት ከአይሂዳ እስከ ጃን ሜዳ (ከ34 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም)" በሚል ርዕስ የዚህ ጥናት አቅራቢ የሆኑት ሰሎሞን ተሾመ (2013 ዓ.ም) በ"ታዛ" ወርሃዊ መጽሔት ላይ ጽሑፍ አቅርበዋል። በጽሑፉም የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ በአክሱም አይሂዳ በሚባል ስፍራ መከበር ከተጀመረበት ከ34 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በጥምቀት በዓላት ላይ ለውጥ የፈጠሩ ታሪካዊ ሁነቶች ላይ ዳሰሳ ተካሂዷል።

ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በአጥኚው የቀረበውን የ"ታዛ" ወርሃዊ መጽሔት ጽሑፍ መነሻ በማድረግ ጥናቱን ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ባሉት አመታት ላይ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶችን በጊዜ ቅደም ተከተል

በጥልቀት በማጥናት፣ በማስረጃ በማስፋት፣ በንድፈሃሳብ በማስደገፍና በመተንተን የምርምር ስራ እንዲሆን ጥረት የተደረገበት ነው፡፡

የጥምቀት በዓል የአከባበር ስርዓትና ስርዓተ ጥምቀትን የሚገልጹ በወርሃዊ መጽሔት ላይ የቀረቡ የዳሰሳ ጽሑፎች አሉ፡፡ ነገር ግን አጥኚው እስከሚያውቀው ድረስ በጃን ሜዳ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶችን በጊዜ ቅደም ተከተል በመግለጽ በወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ የሚያሳይ የምርምር ስራ አለመኖሩ ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ በታች የተገለጹትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በጃን ሜዳ ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በተከበሩት የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶች ምን ምን ናቸው?
- በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱ አበይት ታሪካዊ ሁነቶች በጥምቀት በዓል ላይ ምን ተጽዕኖ አመጡ?
- በጃን ሜዳ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶች የዘመኑን መንፈስ ከመግለጽ አንጻር ያላቸው ሚና ምንድን ነው?

## 2. ጽንሰሃሳባዊ እና ንድፈሃሳባዊ ዳሰሳ

ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በጃን ሜዳ የተከበሩት የጥምቀት በዓላት ላይ በየዘመኑ የተከሰቱ አበይት ሁነቶች ምን እንደሆኑና ሁነቶቹ የዘመኑን መንፈስ ከማሳየት አንጻር ያላቸውን ሚና የሚመረምረው ይህ ጥናት በቃላዊ ታሪክ (Oral History) የፎክሎር ጥናት ዘርፍ ስር የሚመደብ ነው፡፡ ቃላዊ ታሪክ፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ መተዋወቅ የተጀመረው በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ ነው (Allison,1997)፡፡ ቃላዊ ታሪክ፣ በስነ ቃል የፎክሎር ዘውግ ስር የሚመደብ ሲሆን፣ በቃል የሚተላለፉ የግለሰብ፣ የቤተሰብ ወይም የማህበረሰብ ታሪኮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚያጠና የጥናት ዘርፍ ነው (ሰሎሞን፣ 2007 ዓ.ም)፡፡

የቃላዊ ታሪክ ምንነትን በሚመለከት ከቀረቡ የዘርፉ ምሁራን ብያኔዎች መካከል፤ "ቃላዊ ታሪክ በሰዎች ዙሪያ የተገነባ ታሪክ ነው፡፡ ታሪኩም፣ ያለፈና ጠቃሚ የሆነ ሁነትን በትረካ መልክ በቃልና ከጽሑፍ ማስረጃዎች በማመሳከር የሚገለጽበት ነው፡፡" በማለት Saltzman (1997፡452) ሲገልጹ በተመሳሳይም Vansina (1985)፡፡ "ቃላዊ ታሪክ የዘመን ትውስታ ሲሆን፣ በቃላዊ ታሪክ የሚሰበሰቡትና የሚገለጹ ጉዳዮች በመረጃ ሰጪው ግለሰብ የሕይወት ዘመን ተመክሮ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸው ናቸው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በቃል ታሪክ ጥናት ዘርፍ መረጃዎች ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ በጽሑፍ የሰፈሩ የታሪክ መረጃዎች እንደ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ይውላሉ (Burnett, 1977)፡፡ የጽሑፍ መረጃዎቹ እንደ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉት አንድ ሁነት ሲፈጸም የነበረና የሁነቱ ተሳታፊ የነበረ ግለሰብ የጻፈው ማስታወሻ፣ በወቅቱ

የታተሙ የጋዜጣ ወይም የመጽሔት ዜና ወይም ዝርዝር ዘገባ፣ የሕይወት ታሪክ ጽሑፍ፣ የዕለት ተዕለት ገጠመኝ ማስታወሻ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ የመረጃ ምንጮች እንደ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የምንጠቀማቸው በሁለተኛ አካል ያልተላለፉ፣ ያልተለወጡና በወቅቱ የተሰነዱ መሆን እንዳለባቸው (Burnett, 1977) ይገልጻሉ። በተመሳሳይም Thompson (1978) ቃላዊ ታሪክ ስናጠና በቃል ከሚተላለፉ መረጃዎች በተጨማሪ የጽሑፍ መረጃዎች በማስረጃነት መውሰድ እንደሚገባ ይገልጻሉ።

ቃላዊ ታሪክ ከሌሎች የጥናት ዘርፎች የሚለይባቸው፣ በግለታሪክና በታሪክ፣ በግለሰብ ልምድና በማህበረሰብ ለውጥ መካከል ያለውን ተዛምዶ የምንፈትሽበት መሆኑ ነው። ይህም ቃለ ታሪክ፤ ከግለሰብ ገጠመኝና ከግለሰብ ሚና መነሻነት የሕዝባዊ ሁነቶች (public events) የታሪክ ሂደትን የሚያሳውቀንና ግንዛቤ የሚፈጥርልን በመሆኑ ነው (Alessandro, 1997)።

በአንድ ወቅት የተከሰቱ ሕዝባዊ ሁነቶች የታሪክ ሂደት፤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ኃይማታዊ ጉዳዮችን የሚያሳዩ ናቸው። በመሆኑም በወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ (Zeitgeist) እንድንረዳ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው (ሰሎሞን፣ 2007 ዓ.ም)። የዘመን መንፈስ፣ ጽንሰሃሳቡ በዋናነት በተወሰነ ዘመን ውስጥ የተከናወኑና የሆኑ ነገሮችን ራሳቸውን ሳይሆን ነገሮቹ በሰው ልቡና ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ይመለከታል (ቴዎድሮስ፣ 2000 ዓ.ም)።

ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ባሉት አመታት በአዲስ አበባ ከተማ፣ በጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶችን ከጊዜ ቅደም ተከተል የሚያሳየው ይህ ጥናት "ኦራላይዝድ ሂስትሪ" (Oralized History) የንድፈሃሳብ መንገድን የተከተለ ነው። ይህ ንድፈሃሳብ በጽሑፍ የቀረበ ታሪክን እና በጽሑፍ ያልቀረበ ቃላዊ ታሪክን በማጣመር፣ ታሪክን እንደ ንግግር በትረካ ቅርጽ የማቅረብ መንገድ ነው። የዚህ ንድፈሃሳብ አብይ ግብ የታሪክና የቃለ ታሪክ ባህርያትን በማጣመር አንድ ሁነትን መግለጽ ነው (Hamer, 2000)።

"ኦራላይዝድ ሂስትሪ" ንድፈሃሳብ በመደበኛ የጊዜ ቅደም ተከተል (chronology) መሰረት የተከሰቱ ታሪኮች ያላቸውን ዕውነታ በማስረጃ የሚያቀርብ ነው። ይህ ባህሪው፤ ከጽሑፍ ታሪክ የወሰደው ነው (Hamer, 2000)። ይህ ንድፈሃሳብ ጉልህ ከሆኑ ገጠመኞች ውጪ ላሉ ለእያንዳንዱ ሁነቶች ትክክለኛ የሆነ ቀንና ድርጊት በዝርዝር አያቀርብም። ጉልህ ገጠመኞችም ግለሰቦች በማህበረሰብና በህዝባዊ ሁነቶች የታሪክ ሂደት ውስጥ ከስሜታቸው ጋር ቅርብ ቁርኝት ያላቸውና በይበልጥ የሚያስታውሷቸው ናቸው። ይህ ባህሪው ደግሞ ከቃለ ታሪክ የወሰደው ነው (Hamer, 2000)።

በዚህ ንድፈሃሳብ መሰረት የሚቀርቡ ታሪኮች በመዋቅራቸውና በአቀራረባቸው የሚተረኩ (reported) ብቻ ሳይሆን የሚከወኑ (performed) ጭምር ናቸው (Hamer, 2000)። በአንድ ወቅት የተከሰተ ድርጊትን በቅደም ተከተል ከመግለጽና ከመተረክ

ባለፈ የድርጊቱን ክወና፣ የአከዋወኑን መልክ፣ የከዋኙን ማንነት፣ የከዋኙን ማህበራዊ ደረጃና የክወናውን ልዩ ገጽታ ማሳየቱ የወቅቱን አጠቃላይ አካባቢያዊ፣ ማህበረሰባዊና ሀገራዊ ሁነት ያለውን ትርጓሜ በጥልቀት ለመረዳት ይጠቅማል በማለት Hamer (2000) ይገልጻሉ፡፡

ይህ ጥናት "ኦራላይዝድ ሂስትሪ" ንድፈሃሳብን መሰረት በማድረግ ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በጃንሜዳ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አበይት ሁነቶች፣ በበዓሉ ላይ የሀገር መሪዎች የነበራቸው ሚና፣ ጥምቀት የነበረው ልዩ ማህበራዊ መድረክነት፣ በየዘመኑ የተከሰቱ ልዩ ገጠመኞች፣ በሀገሪቱ ውስጥ የተከሰቱ ዋና ዋና የታሪክ ሁነቶች በጥምቀት በዓል ላይ የፈጠሩት አዲስ የአከባበር ስርዓት ለውጥ እንዲሁም በነባሩ ስርዓት ላይ የፈጠሩት ተጽዕኖና መሰል ጉዳዮች በትንተና አሳይቷል፡፡ በጥናቱም መደበኛ የጊዜ ቅደም ተከተልን መሰረት በማድረግ፣ ለታሪኮቹ ተጨባጭ ማስረጃ በማቅረብ፣ ግለሰቦች በበዓሉ ወቅት ከስሜታቸው ጋር ቅርብ ቁርኝት ያላቸውና በይበልጥ የሚያስታውሷቸውን ልዩ ሁነቶች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 3. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ከመስክ ስራ (Field work) ነው፡፡ በመስክ ስራ ወቅት መረጃዎች ከሚሰበሰቡባቸው መካከል ቃለመጠይቅ አንዱ ነው (Goldstein,1964)። በቃል ታሪክ ጥናት ወቅት ቃለ መጠይቅ ትኩረት የሚያደርገው ትናንት የነበሩ እና አሁንም ያሉ ዋና ጉዳዮችና አስተሳሰቦች ላይ ሲሆኑ፣ ሂደቱም ጥያቄ በመስጠትና ምላሽ በመቀበል ላይ እንደሚያተኩር Janesick (2010) ይገልጻሉ፡፡

ቃለመጠይቅ 'ዝግ' (Structured) እና 'ልቅ' (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች ይዋቀራል (Kothari, 2004)። በዚህ ጥናት 'ልቅ' የቃለመጠይቅ ስልትን መሰረት በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች ብዛት ስምንት ናቸው፡፡ በቃለመጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ጥምቀት፣ በድሮው ዘመን እንዴት ይከበር እንደነበር፣ በበዓሉ ላይ የተከሰቱ ልዩ አጋጣሚዎች ምን እንደነበሩ፣ በበዓሉ ላይ በተለየ የሚያስታውሱት ገጠመኝ ምን እንደሆነና መሰል ጉዳዮች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም በጃን ሜዳ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ነገር ግን በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች የሚያስታውሱት ከ1940ዎቹ ጀምሮ የተከበሩትን የጥምቀት በዓላት ነው፡፡ ከ1940ዎቹ በፊት የተከበሩ የጥምቀት በዓላትን በስፍራው በመገኘት ያከበረ ግለሰብ ማግኘትና ቃለመጠይቅ ማድረግ አልቻልኩም፡፡ ይህም የጥናቱ ውስንነት ነው፡፡

ይህ ጥናት ከቃለመጠይቅ፤ በተጨማሪ የንጥል ሁነት ማሳያ ዘዴን (Case study) ተጠቅሟል፡፡ ይህ ዘዴ አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ሲሆን፣ በነጠላ ወይም

አነስተኛ ቁጥር ባለው ተፈጥሯዊ መቼት አማካኝነት ማህበራዊ ሁነቶችን በጥልቀት ለመረዳት የሚጠቅም ነው (Kothari, 2004)። ይህ ዘዴም ጥቂት ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ ድርጊቶችን፣ የክወና አንጓዎችን (Episodes)፣ ሁነቶችን ወይም ውስን ቦታዎችን መሰረት በማድረግ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥልቅ መረጃ ለማግኘት፣ ውስን መረጃዎች ያላቸውን ልዩነቶችና ተመሳስሎ እንዲሁም ያላቸውን ሕብርና አጠቃላይነት በጥልቀትና በስፋት ለመረዳት ይጠቅማል በማለት Bloor and Wood (2006) ይገልጻሉ።

ይህ ጥናት የንጥል ሁነት ማሳያ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን መሰረት በማድረግ የጥምቀት በዓል በሚከበርበትና የጥናቱ ትኩረት በሆነው የጃን ሜዳ ስፍራ ጋር በተገናኘ የግለሰቦች ልዩ የህይወት ገጠመኞች፣ በስፍራው ጥምቀትን ማክበር መቼ እንደጀመሩ፣ ግለሰቦች በጃን ሜዳ የጥምቀት በዓልን ለአመታት ሲያከብሩ ያስተዋሉት አዳዲስ ለውጦች ምን እንደሆኑ፣ እንዴት ወደ ስፍራው መምጣት እንደጀመሩ፣ በቦታው ላይ ያላቸው እሳቤ ምን እንደሆነ፣ ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ባሉት ሀምሳ አመታት በጃን ሜዳ በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ ስርዓተ ጥምቀቱ እንዴት ይከበር እንደነበር፣ በስፍራው ያሉ ግንባታዎች ታሪክና መሰል ጉዳዮችን መርምሯል።

በካልዓይ መረጃዎች ደግሞ በሰነድ የሚገኙ ናቸው። ይህ ጥናት በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ብዙሃን የሚገኙ የመረጃ ምንጮችን በግብዓትነት በመጠቀም በጥምቀት በዓል ምንነት፣ በበዓሉ የአከባበር ስርዓት ላይ በየዘመኑ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች፣ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ በጃን ሜዳ በመገኘት የጥምቀት በዓል የሚያከብሩበትን ስርዓትና ለንጉሱ የሚደረግላቸው መንግስታዊና ሕዝባዊ አጀብ ምን መልክ እንደነበረው፣ ጃን ሜዳ ከጥምቀት በዓል ጋር ያለው የታሪክ ትስስር፣ በጥምቀት በዓል የአከባበር ስርዓት፣ በወቅቱ በሀገሪቱ የተከሰቱ አበይት ታሪካዊ ሁነቶች እንዲሁም በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎችን በምንጭነት በመጠቀም የተሰራ ነው።

## 4- በንግሥት ዘውዲቱ እና በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዘመን በጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች፤በጃን ሜዳ

ልጅ እያሱ ከስልጣን ከተነሱ በኋላ ንግሥት ዘውዲቱ የካቲት 4፣ 1909 ዓ.ም ስርዓተ ንግስና ፈጸው፤ ልዑል ተፈሪም አልጋወራሽ ተባሉ (መርስዔ ኀዘን፣ 2002 ዓ.ም)። በንግሥት ዘውዲቱና በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዘመነ መንግስት የጥምቀት በዓል በጃን ሜዳ እንዴት ይከበር እንደነበርና በዘመኑ ምን መልክ እንደነበረው የታሪክ ምስክር የሆነው የመረጃ ምንጭ "ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ" ነው። ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መታተም ከጀመረበት ከ1917 ዓ.ም ጀምሮ የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓልን በሚመለከት በየአመቱ ሰፊ ዘገባ ያቀርባል።

በጋዜጣ በቀረቡ ሁሉም ዘገባዎች በጃን ሜዳ የጥምቀት በዓላት ላይ የሚገኙት አልጋወራሽ ተፈሪ መኰንን ብቻ ናቸው። በጋዜጣው ንግሥት ዘውዲቱ በጃን ሜዳ

የጥምቀት በዓል ላይ መገኘታቸውን የሚገልጽ ምንም አይነት ዘገባ አልተሰራም። ንግሥት ዘውዲቱ የስኳር ሕመም እንዳለባቸው መርስዔ ኀዘን (2002 ዓ.ም) ይገልጻሉ። ንግሥቲቱ በሕዝባዊ በዓላት ላይ የማይገኙት በስኳር ሕመማቸው ምክንያት ይሁን አይሁን ማወቅ ባይቻልም፤ ንግሥት ዘውዲቱ ለሕዝባዊ በዓላትም ይሁን ለጥምቀት በዓል ጃን ሜዳ ስለመገኘታቸው በጋዜጦች ላይ አልተገለጸም።

በዚህ ዘመን የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓላት እንዴት ይከበር እንደነበር፣ በየጊዜው የተከሰቱ አዳዲስ ሕዝባዊ ሁነቶችን እንዲሁም የወቅቱ የዘመን መንፈስ ምን መልክ እንዳለው ቀጥለን እንመልከት።

ጥር 10 ቀን፣ የከተራ ዕለት በየቤተክርስቲያኑ ያሉ ታቦታት በሊቀ ጳጳሳት፣ በቀሳውስት፣ በዲያቆናት፣ በካህናትና በምዕመናን ዝማሬ፣ በሕዝቡ ዘፈንና ሆታ ታጅበው ወደ ማደሪያ ቦታቸው ጃን ሜዳ ይሄዳሉ። በዚህ እለት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የጥምቀት በዓልን ለማክበር ታቦታትን ከኋላ አጅበው ወደ ጃን ሜዳ ይሄዳሉ። በማግስቱም ጥር 11 ጃን ሜዳ በመሄድ ታቦታትን አጅበው ይመለሳሉ (ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ፣ 1917 ዓ.ም)። ጥር 12፣ የመልዐኩ ቅዱስ ሚካኤልና የቃና ዘገሊላ የመታሰቢያ ዕለት ነው። በዕለቱም አልጋ ወራሽ በመኳንንትና መሳፍንት ታጀበው በደማቅ ስርዓት በጃን ሜዳ የቀበና ወንዝ የሚያድረውን የየካ ሚካኤል ታቦትን አጅበው ከቤተክርስቲያኑ ያስገባሉ።


በወቅቱ ታቦታት ወደ ጃን ሜዳ ሲሄዱ፣ ከፊት ለፊት በርካታ ቁጥር ያለው ወታደር፣ በወታደራዊ ልብስ አምሮና አጊጦ በሰልፍ ይሄዳል። ከወታደሮቹ ቀጥሎም በወቅቱ "ሰይፈ ጃግሬ" በመባል የሚጠሩ የክቡር ዘበኛ አንጋቾች ይከተላሉ። ሰይፈ ጃግሬዎች ወታደራዊ ልብስ ለብሰው፣ ጠመንጃቸውን በቀይ መለዮ አስጊጠው በሰልፍ ይሄዳሉ። ከሰይፈ ጃግሬዎች ቀጥሎም ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን፣ ቀሳውስቱና ዲያቆናት የወርቅ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ታቦታትን ይዘው በመካከል ይሄዳሉ (ብርሃንና ሰላም፣1917 ዓ.ም)።

ከቀሳውስቱና ከዲያቆናት ቀጥሎ አልጋ ወራሽ ይከተላሉ። አልጋ ወራሽ ጃን ሜዳ ሲሄዱ፣ የወርቅ እቃ ባስጨነቃት በቅሎ ተቀምጠው ነው። እሳቸው በሚሄዱበት ወቅት ፀሐይ ወይም ዝናብ እንዳይመታቸው እንዲሁም ክብራቸውን ለመግለጽ በወርቅ ሙካሽ የተሰራ፣ ባለ ወርቅ አጫዋች ያለው፣ በልዩ ዲዛይን የተሰራና ለነገስታት የሚገባ ቀይ ጥላ አስይዘው ነው። ለጃንሆይ የሚያዘው ጥላ ባለወርቅ መርገፍ ግምጃ ጥላ በመባል ይጠራል። ጥላ ያዥውም ጥላውን ወደ ላይ ክንድ ያህል ከፍ አድርጎ ይይዛል። ክቡራን መኳንንት እንደ ማዕረጋቸው ራቅ ራቅ ብለው ልዑሉን አጅበው ይጓዛሉ (ብርሃንና ሰላም፣1917 ዓ.ም)። በ1917 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አስራ ሰባት አድባራት እንደ ልማዳቸው በየአካባቢያቸው በሚገኝ ወንዝ ወርደው የጥምቀት በዓልን ያከበሩ ሲሆን፣ በጃን ሜዳ የመጡ አድባራት አምስት ናቸው (ብርሃንና ሰላም፣1917 ዓ.ም)።

በዚህ አመት የተከበረውን የጥምቀት በዓል ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (1917 ዓ.ም) የጥምቀት በዓልን ለማክበር ዘበኛ ወታደር ከልዑሉ በግራና በቀኝ እንደ አጥር ሆኖ

ወደ ጃን ሜዳ ሲጓዝ፣ የኋላ ዘበኛ ግን ሃምሳ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ተደርድሮ ይጓዝ ነበር። በጅሮንድ ሣህለ ድንግል መለዮ የለበሱ ስልሳ ስድስት ዘበኛና ሌላም ብዙ ወታደር፣ ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ጋሪ ጭፍሮቻቸውንና የመትረየስ ዘበኞችን፣ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዘአማኑኤል የአራዳን ዘበኛን አሰልፈው ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ጃን ሜዳ የሚመጡ አድባራትን አጅበው ጃን ሜዳ ተቀላቀሉ። በዚህን ጊዜ ጃን ሜዳ በሰራዊት ተጨናንቆ መተንፈሻ አጣ በማለት ዘግቧል።

በ1917 ዓ.ም በዘመናዊ የሰልፍ ትምህርት የሰለጠነው የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ የመትረየስ ዘበኛ የተባለው ጭፍራ በአለቃው በግራዝማች ገብረ ዮሐንስ እግር ተሰልፎ አምሮ ለጥምቀት በዓል ወደ ጃን ሜዳ መጣ። አልጋ ወራሽ በቅሎ ላይ ሆነው በቀኝ መትረየስ አንጋች ዘበኛ ወታደር በዘመናዊ የሰልፍ ስርዓት ሰማያዊ ኮት ለብሶ፣ ነጭ ሱሪ ታጥቆ፣ እምቢልታና መለከት እየተነፋ (እየተንጠረጠረ)፣ ነጋሪትም እየተጎሸመ ይታጀባሉ። በወቅቱ ነጋሪት መችዎች ቀይ ኮት የሚለብሱ፣ ቀይ ጃዊ የሚጠመጥሙ ናቸው። ነጋሪት መችዎችም ከፊት ለፊት ሁለት ሰንደቅ ዓላማ ይይዛሉ (ብርሃንና ሰላም፣1917 ዓ.ም)።



ፎቶ 1፡- የ1917 ዓ.ም አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን የቃና ዘገሊላ በዓል ሲያከብሩ የሚያሳይ (ምንጭ፡ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ፣1917 ዓ.ም)

የመትረየስ ዘበኛ ወታደሮች የደንብ ልብስ ኮት ነበር። ይህ አለባበስ ለሕዝቡ አዲስ ክስተት ነበር። የዚያ ዘመን ኮት መልበስ እንደ ነውር ይቆጠር ነበር። ኮት መልበስ ነውርና አሳፋሪ ነገር አለመሆኑን ልዑል አልጋ ወራሽ ዘመናዊ ሰልፍ ትምህርት ተምረው የሰለጠኑ የአዲስ አበባ ከተማ ዘበኞችና የልዑል አልጋ ወራሽ የመትረየስ ዘበኞች መስከረም 30 ቀን፣ 1917 ዓ.ም በፍልውኃ ሜዳ ለአልጋ ወራሽ ትልቅ ሰልፍ ባሳዩበት በንግግራቸው ማሳሰባቸውን መርስዔ ኀዘን (2002 ዓ.ም) ገልጸዋል።

በጥር 11 ቀን፣ 1917 ዓ.ም በተከበረው የጃን ሜዳ ጥምቀት በዓል ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ዘበኞችና የመትረየስ ዘበኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ኮት ለብሰው በጃን ሜዳ የሰልፍ ትርኢት ያደረጉበት አመት ነበር፡፡

አልጋ ወራሽ ታቦታትን ጃን ሜዳ አድርሰው በተመሳሳይ አጀብ ወደ ቤተመንግስታቸው ይመለሳሉ፡፡ በማግስቱ ጥር 11 በተመሳሳይ አጀብ ወደ ጥምቀተ ባህሩ ይሄዳሉ፡፡ አልጋ ወራሽ ታቦታቱ ወዳሉበት ስፍራ ተመልሰው በተዘጋጀላቸው ከፍ ባለ ስፍራ ይቀመጣሉ፡፡ ንጉሱ በታላቅ ግርማ ሆነው አጎበር ባለው ወንበር ሲቀመጡ በኃይማኖት አባቶችና በመኳንንት ታጅበው ነው፡፡ አልጋ ወራሽ በጃን ሜዳ ልዩ የማረፊያ ስፍራ በድንኳን ይዘጋጅላቸዋል፡፡ በድንኳኑ ውስጥም በመርገፍ የተለየ ልዩ ክፍል ይዘጋጃል፡፡ በክፍሉ ውስጥ ቀይ ምንጣፍ ይነጠፋል፣ ዙሪያውን በአበባ የተሽቆጠቆጠና በአጎበር የተሸፈነ ዙፋን ተዘጋጅቶላቸው እንዲያርፉ ይደረጋል (ብርሃንና ሰላም፣1917 ዓ.ም)፡፡

አልጋ ወራሽ ጥምቀት ላይ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ሲቀመጡ በቤተ ክርስቲያኗ አቡን፣ ብጹዕ አቡነ ማቴዎስ፣ አማካኝነት በመስቀል ተባርከው በዙፋናቸው ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ከእሳቸው በኂላ አጃቢዎቻቸው እንደማዕረጋቸው በቅደም ተከተል በመስቀል ይባረካሉ፡፡ የአልጋ ወራሽ አጃቢዎች በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ሲቀመጡ ያላቸውን ማዕረግ፣ ስልጣንና የቤተሰብ ቀረቤታ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ከአልጋ ወራሽ ተፈሪ ጎን ባለቤታቸው ልዕልት ወይዘሮ መነን፣ በቀኝ በኩል እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ክቡር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስና ሌሎችም መኳንንት አብረዋቸው ይቀመጣሉ፡፡ ከአልጋ ወራሽ አጎበር ፊት ለፊት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ይውለበለባል፡፡ ጥምቀተ ባህሩም በብጹዕ አቡነ ማቴዎስ ይባረካል፡፡ በአቡኑ አማካኝነት ንጉሱና መኳንንቱ ጸበል ከተረጩ በኂላ፣ ኃይማኖታዊ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ታቦታቱም በአጀብ ወደ ቤተክርስቲያናት ይመለሳሉ፡፡

ጥር 12፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ላይ ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ በመቀየር የመጀመሪያ ተአምራቱን የገለጸበት ቀን መታሰቢያ በዓል ነው፡፡ በዕለቱም የቅዱስ ሚካኤል በዓል ስለሆነ ታቦቱ ጥምቀተ ባህር ያድራል፡፡ በዕለቱም አልጋ ወራሽና ባለቤታቸው ልዕልት ወይዘሮ መነን ከመኳንንቱ ጋር በብዙ ሰራዊት ታጅበው የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት ቤተክርስቲያኑ ድረስ አስገብተው ይመለሳሉ፡፡ በዚህ ዕለት ፈረሰኞች በጃን ሜዳ በመገኘት የጉግስ ጨዋታና የግልቢያ ውድድር ያደርጉ ነበር፡፡

በ1918 ዓ.ም በጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ሲከወን በስፍራው የተገኙት አድባራት ስድስት ነበሩ፡፡ በዚህ ወቅት ታቦታት ያድሩ የነበረው በቀበና ወንዝ ነው፡፡ ጥምቀቱም ይካሄድ የነበረው በወንዙ ዳር ነበር፡፡ በዚህ አመትም፣ ሊጋባ ወዳጄ፣ የግቢ ዘበኛ አለቃ ፊታውራሪ ገብረ ማርያም፣ ባሻ ግዛው፣ አጋፋሪ ወልደ ማርያምና ግራዝማች ከልክሌ ከተከታዮቻቸው ጋር እንደ ማዕረጋቸው ሽልማታቸውን ለብሰው፣ ክንዳቸውን አውጥተው፣ ዘንጋቸውን ይዘው፣ ጠመንጃቸውን አንግተው፣ ጎራዴያቸውን

ታጥቀው ስርዓቱን መርተዋል (ብርሃንና ሰላም፣ 1918 ዓ.ም)። በዚህ አመት በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይም ሁለት ባሕታዊያን እርስ በርሳቸው አምባ ጓሮ አንስተው በዱላ ሲማቱ ዘበኛ እንደያዛቸው ብርሃንና ሰላማ ጋዜጣ (1918 ዓ.ም) ዘግቧል።

ቀደም ሲል ከተከበሩ በዓላት የ1918 ዓ.ም የጥምቀት በዓልን ልዩ የሚያደርገው ሁኔታ ተፈጽሞ ነበር። ይህም አለቃ ኢዮብ ያስተማራቸው ፈረሰኞች ነጭ ኮት፣ ነጭ ባርኔጣ አድርገው ባማረ ሰልፍ ተሰልፈው ለአልጋ ወራሽ በጡሩንባ የክብር ሰላምታ መስጠታቸው ነበር (ብርሃንና ሰላም፣ 1918 ዓ.ም)። በዚህ መልክ ሰላምታ የመስጠት ልምድ ስላልነበር በሕዝቡ ዘንድ ልዩ አግራሞትና መደነቅ የፈጠረ ሲሆን ለበዓሉም ድምቀት መፍጠሩን ጋዜጣው ጨምሮ ዘግቧል። የበጥምቀት በዓል ወቅት ካህናቱና ሊቃውንቱ የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው በስርዓት በመቆም ‹‹ሃሌ ሃሌ ሃሌሉያ ተጠምቀ ሰማያዊ በእደመሬታዊ" እያሉ ይወርባሉ።

በታህሳስ ወር 1915 ዓ.ም ብጹዕ አቡነ ማቴዎስ በጤና መታወክ ምክንያት ወደ ምድረ ግብጽ ሄደው አስር ወራት ያህል ሲታከሙ ቆይተው ጥቅምት 27 ቀን 1916 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመለሰው እንደነበር መርስዔ ኀዘን (2002 ዓ.ም) ይገልጻሉ። በ1918 ዓ.ም አቡነ ማቴዎስ በድጋሚ ሕመም ገጠማቸው። በሕመማቸውም ምክንያት በ1918 ዓ.ም በተከበረው የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ላይ አልተገኙም። በእሳቸው ምትክ በዓሉን በበላይነት የመሩትና ለምዕመናን ወንዙን ባርከው የረጩት ብጹዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው (ብርሃንና ሰላም፣ 1918 ዓ.ም)።

በህዳር 25 ቀን፣ 1919 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ አረፉ (መርስዔ ኀዘን፣ 2002 ዓ.ም)። በዚህ ዓመት በተከበረው የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ማቴዎስ ባረፉ ከወራት በኋላ የተከበረ የጥምቀት በአል መሆኑ በወቅቱ የነበረው ሀዘን አዲስ ክስተት ነው። በዚህ አመትም ወንዙን ባርከው የረጩት ብጹዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (1919 ዓ.ም፣23) ጥምቀት የሚካድበትና ጸበል የሚረጭበት የቀበና ወንዝን በሚመለከት "ለእንግዲሁ ግን ከሱ በተሻለ ወንዝና የጠራ ብዙ ውኃ ባለበት ቢደረግ ለሚጠቀመው ሕዝብ ሁሉ እጅግ ይበልጥ ደስ ባሰኘ።" በማለት አስተያየት ሰጥቶ ነበር።

በሰኔ 21 ቀን፣ 1921 ዓ.ም አቡነ ቄርሎስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሹመው ከግብጽ አዲስ አበባ ገቡ (መርስዔ ኀዘን፣ 2002 ዓ.ም)። አቡነ ቄርሎስ በተሾሙ በቀጣይ አመት በ1922 ዓ.ም የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓልን በበላይነት የመሩና ለምዕመናን ጸበል የረጩት ብጹዕ አቡነ አብርሃም ናቸው (ብርሃንና ሰላም፣ 1922 ዓ.ም)።

ቀሳውስትና ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው፣ አቡኖቹ ያማረ በቅሎ ተቀምጠው ታቦታትን አጅበው ይሄዱ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኮንን ባማረች በቅሎ ተቀምጠው ከፍ ብለው ይታዩ እንደነበርና ሙዚቀኛ ወታደሮች ባማረ ሰልፍ ተሰልፈው ሙዚቃ ማሰማታቸው ብርሃንና ሰላም (1922 ዓ.ም) ዘግቧል። ከሌሎች ቀደምት አመታት በተለየ በዚህ አመት በተከበረው

የጥምቀት በዓል ላይ አቡኖቹ በበቅሎ ተቀምጠው ታቦታትን ማጀባቸውና ወታደሮች ሙዚቃ ማቅረባቸው አዲስ ሁነቶች እንደነበሩ ከጋዜጣው ዘገባ እንረዳለን፡፡

በዚህ ዘመን የጥምቀት በዓል አከባበር ሂደትና የነበረው ድምቀት ምን ይመስል እንደነበር እምሩ (2015 ዓ.ም፣ 52)

> በሕዝብ በዓላት ቀናት ትርዒትና ሠልፉ ለትንግርት ነበር፡፡ በተለይ የጥምቀት በዓል አከባበር በጣም ደማቅ ነበር፡፡ አንድ ቀን አባቴ በዓሉ ወደሚከበርበት ጃንሜዳ ይዘውኝ ሄዱ፤ ንጉሠ ነገሥቱና ቤተሰባቸው፣ ፓትሪያርኩ፣ አቡኖቹ እና መኳንንቱ እስከነ አጃቢዎቻቸው በዚያ ነበሩ፡ ሁላቸውም የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ነበር፡፡ ብዙኃኑ ባህላዊ ልብሶቻቸውን በእንዶድ አጥበው አምረው ነበር፡፡ ነጫጮቹ የብዙኃኑ ልብሶች በወርቅና ብር ከተጌጡቱ ከፍተኛ ባለሥላጣኖችና ሌሎች ጨዋዎች ከለበሷቸው ከባለ ላንቃዎች የተለየ መልክ ይዘው ይታዩ ነበር፡፡ የፈረሶቹና የበቅሎዎቹ ኮርቻዎችና ልጓሞች ሳይቀር እጅግ የተጌጡ ነበሩ፡፡ በወርቅና በብር የተለበጡ የጃንሜዳ አረንጓዴ ሣርና በስተጀርባ የሚታየው የእንጦጦ ጋራ ልምላሜ ትርዒት ታክሎበት ትዕይንቱ እጅግ አስደናቂ ውበት ነበረው፡፡ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በመጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ አረፉ፡፡ በማግስቱ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በንጉሠ ነገሥት ዙፋን ተቀመጡ፡፡ ስማቸውም ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ ተብሎ መሰየሙ በግልጽ ተነገረ (መርስዔ ኀዘን፣ 2002 ዓ.ም፣409)፡፡ ከዚህ በመቀጠል በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመን በጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ ሁነቶች ምን ምን እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡

## 5- በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመን በጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች፤በጃን ሜዳ

አልጋ ወራሽ ተፈሪ፣ በጥቅምት 23 ቀን በ1923 ዓ.ም የዘውድ ስርዓት ፈጽመው ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ፡፡ በዚህ አመት የተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ፈረሰኞች ጉግስ ይጫወቱ እንደነበርና በጨዋታውም የተጎዱ መኖራቸውን ጫወታውም ሕገ ወንጌልና ሕገ ኦሪት ለመዋጋታቸው ምሳሌ መሆኑን በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (1923 ዓ.ም) ተዘግቧል፡፡

ከቀደምት አመታት በተለየ በዚህ አመት በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ፈረሰኞች የጉግስ ስለመጫወታቸው አዲስ ክስተት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ከዚህ በፊት ያደርግ እንደነበረው የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል የአከባበር ሂደት ላይ ዘገባ ከመስራት ይልቅ ስለገሃድ ጾም፣ ስለጥምቀት፣ ስለቃና ዘገሊላ ምንነት ላይ ያተኮረ ዘገባ ማቅረቡና ስለንጉስ አጀብና በስፍራው ተገኝተው የጥምቀት በዓል ስለማክበራቸው ምንም አይነት መረጃ አልሰጠም፡፡ እነዚህ አዳዲስ ሁነቶች የዚህን አመት የጥምቀት በዓል አከባበር የተለየ ያደርጋቸዋል፡፡

በ1924 ዓ.ም በጃን ሜዳ የተከበረው የጥምቀት በዓል የተለየ ክስተት የተፈጠረበት ነበር፡፡ ይህም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በበዓሉ ላይ አለመገኘታቸው ነበር፡፡ ንጉሱ

በስፍራው ያልተገኙትም የጤና ችግር ስላጋጠማቸውና ወደ ውጪ እንዳይወጡ በሀኪማቸው ስለተከለከሉ ነው። በዚህ አመት የተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ንጉሱ መታመማቸው ስለተሰማና ለበዓሉም በጃን ሜዳ ስላልተገኙ በወቅቱ የነበረውን የጥምቀት በዓል ድባብ "ይገርማል የጥምቀትና የቃና ዘገሊላ ዕለት መኳንንቱና ሠራዊቱ ሕዝቡም ልክ እንደቀድሞው ተሰብስበው ነበር። ሊቃውንቱና ካህናቱም እንደቀድሞው ይዘምሩ ነበር። ነገር ግን አውራ የሌለው ንብ መስሎ ቀዝቅዞ ዋለ እንጂ ቢዘመር ቢዘፈንም እንደ ቀድሞው አልደመቀም።" በማለት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (1924 ዓ.ም፤1) ዘግቧል።

በ1925 ዓ.ም በጃን ሜዳ የተከበረውን የጥምቀት በዓል ያሳረጉት የአዲስ አበባ ሥላሴ መምህር የሆኑት ገብረ ሚካኤል ናቸው (ብርሃንና ሰላም፣ 1925 ዓ.ም)። በጥምቀት ማግስት በሚከበረው የቅዱስ ሚካኤልና የቃና ዘገሊላ መታሰቢያ ዕለት አጼ ኃይለሥላሴ ጃን ሜዳ ቀበና ወንዝ የሚያድረውን የየካ ሚካኤል ታቦት ካስገቡ በኋላ ግብር ያበላሉ። በ1925 ዓ.ም በተከበረው የቃና ዘገሊላ ዕለት ግን ንጉሱ ግብር ሳያበሉ ቀርተዋል። ለዚህም ምክንያቱ ቃና ዘገሊላ በዕለተ አርብ ስለዋለና የጾም ቀን በመሆኑ በሶስተኛው ቀን እሁድ ግብር እንደተደረገ ብርሃንና ሰላም (1925 ዓ.ም) ይገልጻል።

በ1926 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባማረ በወርቅ መረ ሻት ያጌጠች በቅሎ ተቀምጠው በታላላቅ መኳንንት፣ አርበኞች፣ ሚኒስትሮች፣ የከተማው ታላላቅ የሮፓ (የአውሮፓ) ሰዎች፣ የውጭ ሀገር የዲፕሎማሲ ሰዎች፣ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ታጅበው በታላቅ ሰልፍ ታቦታትን አጅበው ወደ ጥምቀተ ባህሩ እንደሄዱ አዕምሮ ጋዜጣ (1926 ዓ.ም) ዘግቧል። በመሳሳይም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጃን ሜዳ መሐከል በተተከለው ድንኳን ውስጥ በተዘጋጀላቸው መንበረ መንግስት ተቀምጠው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና የኢትዮጵያ መሳፍንት፣ የውጭ አገር መንግስታት ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ሌሎችም በከተማው የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች በግራና በቀኝ ተቀምጠው እንደነበር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (1926 ዓ.ም) ዘግቧል።

ከዚህ በፊት በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ በሚወጡ የጋዜጣ ዘገባዎች ላይ የውጭ ሀገር ዲፕሎማሲዎችና የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ታላላቅ ሰዎች ለጥምቀት በዓል መገኘት ወይም አለመገኘታቸውን በሚመለከት ምንም አይነት ዘገባ አይሰራም ነበር። ዲፕሎማቶችና የውጭ አገር ዜጎችን በሚመለከት የተሰራው የጥምቀት ዘገባ ይህ አመት የጥምቀት በዓልን ለመንግስታት የዲፕሎማሲ ግንኙነትና ለሕዝብ ለሕዝብ ትብብር የመጠቀም ስልት የተጀመረበት እንደሆነ መገመት ይቻላል። 1926 ዓ.ም በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ንጉሡ ከመኳንንትና መሳፍንት በተጨማሪ በአርበኞች ታጅበው በታላቅ ሰልፍ ታቦቶችን አጅበው ወደ ጃን ሜዳ መሄዳቸውን አዕምሮ ጋዜጣ (1926 ዓ.ም) ዘግቧል። በመሆኑም የ1926 ዓ.ም የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች፣ ቆንስሎችና አርበኞች መገኘታቸው አዲስ ሁነት ነው። ይህ አዲስ ሁነት ወቅቱ የጦርነት ዋዜማ እንደሆነ አመላካች ነበር።

በ1927 ዓ.ም የተከበረው የጥምቀት በዓል ቀደም ሲል ከተከበሩት በዓላት ሁሉ እጅግ የተቀዛቀዘና የሀዘን ድባብ ያጠላበት ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ጣሊያን ኢትዮጵያን

ለመውረር ጦርነት በመጀመሩ ነው። በዓሉ ከመከበሩ ከአንድ ወር በፊት፣ በታህሳስ ወር ላይ በወልወል ድንበር በኩል የጣሊያን ጦርና የኢትዮጵያ ጦር ውጊያ ጀምረዋል። በሰሜንም የጣሊያን ጦር ድንበር ገፍቶ መግባት ጀምሯል።

ይህም በዚህ ዓመት የተከበረው የጥምቀት በዓል ከዘፈንና ከሆታ ይልቅ የመዝሙር፣ የጸሎትና የምህላ መንፈሳዊ ስርዓቶች ጎልተው የታዩበት ነበር። በጥምቀት ማግስት፣ ጥር 12፣ 1927 ዓ.ም በየካ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ቄርሎስ፣ በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበው የጦርነት አደጋ እንዲቀረፍና የሀገር ሰላም እንዲመለስ ሕዝቡ በጾምና በጸሎት እንዲለምን የአንድ ሳምንት የምህላ ፕሮግራም እንዳወጁ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (1927 ዓ.ም) አስፍሯል። ጋዜጣው ላይም ብጹዕ አቡነ ቄርሎስ በየካ ቅዱስ ሚካኤል የሰበኩት ስብሰከት በሁለት ክፍል በሰፊው ተዘግቧል።

### 6- በጣሊያን ወረራ ወቅት በጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች፤በጃን ሜዳ

የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ላይ ለውጥ ከፈጠሩ ታሪካዊ ሁነቶች መካከል አንዱ የጣሊያን የአምስት አመት ወረራ ነው። ጣሊያን ሀገራችንን በወረረ ወቅት እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ከንጉሱ ጋር ተሰደዱ። በፋሽስት ጣሊያን አማካኝነት አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ተገደሉ። የዝቋላ አቦ ቤተክርስቲያንና የደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቃጠሉ። በርካታ የሀይማኖት አባቶች ሕዝቡ ፋሽስት ጣሊያንን እንዲዋጋና ለሀገር ነጻነት ክብር እንዲፋለም ጥሪ በማድረግ አርበኛ ሲሆኑ፣ በተቃራኒው የተወሰኑ የሀይማኖት አባቶች ለጣሊያን አደሩ።

በፋሽስት ጣሊያን አማካኝነት አቡነ ቄርሎስ እጨጌ ተብለው ተሾሙ (Wudu, 2006፣92)። በጃን ሜዳ በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ታላላቅ የሀይማኖት መሪዎች ህዝቡ ለጣሊያን እንዲያድር ቀሰቀሱ። ቀሳውስቱ ለጣሊያን በመቀስቀሳቸውም የገንዘብና የአልባሳት ስጦታ ያገኙ ነበር። በጣሊያን ሀገርም ጉብኝት ይመቻችላቸው ነበር (Wudu,2006፣102)።

ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በየካቲት 12 ቀን፣ 1929 ዓ.ም በጣሊያኑ የጦር መሪ አልቤርቶ ግራዚያኒ ላይ በተጣለው ቦንብ ቆሰሉ። ወደ ኢጣሊያን ሀገር ለሕክምና ተወስደው ከሕክምናው በኋላ ወደ ሀገራቸው ግብጽ ሄዱ። ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው አልመጡም (መርስዔ ኀዘን፣ 2002 ዓ.ም፣364)። በእሳቸው ምትክ አቡነ አብርሃም እጨጌ ተብለው ተሾሙ።

በጣሊያን ወረራ ወቅት የተለየ አመት እንደሆነ የሚነገረው የ1930 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ነው። በዚህ አመት የሸዋ አርበኞች መሪ ራስ አበበ አረጋይ አቡነ ገብረ ጊዮርጊስን የኢትዮጵያ እጨጌ ብለው መረጡ። በተመሳሳይም አቡነ አብርሃም በማረፋቸው፣ በእሳቸው ምትክ ፋሽስት ጣሊያን አቡነ ዮሐንስንና አቡነ ፊሊፖስን የኢትዮጵያ እጨጌ ብሎ በመስከረም ወር ላይ ሾማቸው (Wudu, 2006)።

በ1930 ዓ.ም በተከበረው የጃን ሜዳ ጥምቀትም ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለት የኢትዮጵያ እጨጌዎች መሪነት የተከበረ ታሪካዊ በዓል እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተመሳሳይም አርበኞቹ ባሉበት አካባቢ አቡነ ገብረ ጊዮርጊስን እጨጌ ብለው በመሾማቸው፣ ኢትዮጵያ በጥቅሉ በሶስት እጨጌዎች እንድትመራ ሆነ (Wudu, 2006)፡፡ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተከበረው የዚህ አመት የጥምቀት በዓልም በሶስት እጨጌዎች የተመራ የመጀመሪያው በዓል ሆኖ ታሪክ መዝግቦታል፡፡



ዲያቆናቱ ፤ አዲሱን ፣ ባንዲራ ፣ ይዘው ፣ ከፊት ፤ እየሔዱ ፣ በጃንሜዳ ፣ የታቦታቱ ፤ ጉዞ ሲደረግ
I DIACONI PORTANO IN PROCESSIONE LE BANDIERE DELLE CHIESE

ፎቶ 2፡- በ1932 ዓ.ም የቤተክርስቲያን ባንዲራ ተይዞ የጥምቀት በዓል በጃን ሜዳ ሲከበር የሚያሳይ (ምንጭ፡ የሮማ ብርሃን ጋዜጣ፣ 1932 ዓ.ም)

በጣሊያን ወረራ ወቅት በ1932 ዓ.ም የጥምቀት በዓል በጃን ሜዳ እንዴት እንደተከበረ የሮማ ብርሃን ጋዜጣ (1932 ዓ.ም) "በማንም ጊዜ ተደርጎ ያልታወቀው የመድኃኒያለም ስዕልና መስቀል ያለበት የቤተክርስቲያን ባንዲራ ለእያንዳንዱ አድባራት ስለተሰጠና ታቦታት ሲወጡ ለማክበር ከጥሩ አይነት ጨርቅ የተሰራ ዳርዳሩን በከፋይ የተከፈፈ አጎበርና ድባብ አዘጋጅቶ መንግስት አድሏል፡፡" በማለት ዘግቧል፡፡ ይህም በወቅቱ በበዓሉ የአከባበር ስርዓት ላይ የተከሰተ አዲስ ሁነት ነው፡፡

በዚህ አመት በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይም በሊቀ ሊቃውንት ገብረመስቀል የተማሩ የአዲስ አበባ ደብረ ሰላም መድኃኒያለም ተማሪዎች ጸዓዳ ልብስ ለብሰው የቤተክርስቲያን ባንዲራ ይዘው በተስተካከለ ሰልፍ ታቦታትን ማጀባቸው በሮማ ብርሃን ጋዜጣ (1932 ዓ.ም) ተዘግቧል፡፡ የዚህ ዓመት የበዓሉ ስርዓትም በአዲስ አበባ ሬዜዴንቲ በዶቶር ባስከዩሪ ተከናውኗል፡፡ ጥምቀተ ባህሩም በሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተባርኮ ለሕዝቦ ጸበል ተረጭቷል፡፡

በወቅቱ የጣሊያን ባለስልጣናትና ሊቀ ጳጳሱ የጥምቀት በዓልን ለማክበር ወደ ጃን ሜዳ ሲመጡ፤ ባለስልጣናት ባውቶሞቢል መኪና፣ ሊቀ ጳጳሱ ደግሞ የወርቅ ዕቃ በተጫነች የወርቅ ድግርግ መረሻት በጎናጸፌች በቅሎ ሆነው የወርቅ ጥላ ተይዞላቸው ነው (የሮማ ብርሃን፣ 1932 ዓ.ም)።

## 7- ከጣሊያን ወረራ በኋላ በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በጥምቀት በዓል ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች፤በጃን ሜዳ

ጥር 12 ቀን፣ 1933 ዓ.ም አጼ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት በስደት ከቆዩበት እንግሊዝ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ታጅበው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በኦሜድላ ሰቀሉ። ኦሜድላ በሱዳን እና በኢትዮጵያ ድንበር ላይ በዲንደር ወንዝ አቅራቢያ የምትገኝ አነስተኛ መንደር ነች። ይህ አመት ኢትዮጵያ ከጣሊያን ወረራ ነጻ የወጣችበትና ንጉሱም ወደ ስልጣናቸው የተመለሱበት በመሆኑ፣ በአመቱ በ1934 ዓ.ም የተከበረው የጥምቀት በዓል ከሌሎች በዓላት በተለየ መልኩ የአርበኞች ሰልፍ፣ ሽለላ፣ ፉከራና ቀረርቶ በጃን ሜዳ በስፋት የታየበት ነበር (ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ፣1934 ዓ.ም)።

በጥምቀት በዓል ማግስት ጥር 12፣ የቃና ዘገሊላ ዕለት፣ የኦሜድላ ድል መታሰቢያ ቀን ተብሎ ተሰየመ። ከቤተመንግስት ወደ የካ ሚካኤል የሚወስደው መንገድ ኦሜድላ መንገድ ተብሎ ተሰየመ። በጥር 12፣ 1934 ዓ.ም የቃና ዘገሊላ ዕለት ንጉሱ የየካ ሚካኤልን ታቦት ለማስገባት ቤተክርስቲያን በተገኙት ወቅት የሕዝቡ ደስታ ከፍ ያለ ነበር። ይህ ዕለት ከነጻነት ድል ጋር በማያያዝ አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1934 ዓ.ም) "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ በሰርግ ቤት ውኃውን ጠጅ ሲያደርግ ተዓምራቱ ደስ ከማሰኘቱና ከማስደነቁ በላይ ጠጅ አልቆበት ተቸግሮ የነበረውን የሰርጉን ባለቤትና እድምተኞቹን ማርካቱ ዘለዓለማዊነት ያለው አምላካዊ ውለታ እንደሆነ፣ እንዲሁም በኦሜድላ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አድሮ ለኢትዮጵያ ያደረገው ተዓምራት በትውልድ መካከል ሳይዘነጋ የሚኖር ነው።" በማለት ዘግቧል።

በ1935 ዓ.ም አጼ ኃይለ ስላሴ ጥምቀት በዓልን ለማክበር ወደ ጃን ሜዳ ሲመጡ በአውቶሞቢል መኪና ሲሆን፣ በሞተር ቢስኪለተኞች ታጅበው ነው። ንጉሱም በስፍራው የተገኙት ከልዑላን መሳፍንት፣ ክቡራን ሚኒስትሮችና መኳንንት እንዲሁም ኮርዲፕሎማቲኮችና ታላላቅ የመንግስት ሰራተኞች ጋር በመሆን ነው (አዲስ ዘመን፣ 1935 ዓ.ም)። በጥምቀት በዓል ላይ ንጉሱ ከውጭ ሀገር ኮርዲፕሎማቶች ጋር መምጣት በ1926 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፣ የንጉሱ በአውቶሞቢል መኪና እና በሞተር ቢስኪለተኞች መታጀብ ግን ከጣሊያን ወረራ በኋላ የተጀመረ አዲስ ልማድ ነው። ይህ መሆኑም በወቅቱ የተከሰተ አዲስ ሁነት ነው።

በ1938 ዓ.ም ለጥምቀት እንዲሆን በጃን ሜዳ ግቢ ውስጥ የውኃ ማጠራቀሚያ የገንዳ ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት የሰጠበት አመት ነው (አዲስ ዘመን፣ 1938 ዓ.ም)። ቀደም ሲል የጥምቀት በዓል በቀበና ወንዝ በተከተረ የውኃ ኩሬ ላይ ይከወን የነበረው የጥምቀት ስርዓት ቀርቶ፣ በጃን ሜዳ ግቢ ውስጥ በተሰራው የውኃ ገንዳ ላይ መከወን ተጀመረ። ይህም ወደ ቀበና ወንዝ የሚደረገውን ጉዞ አስቀርቶ እዛው

ጃን ሜዳ ግቢ ውስጥ ጸበል የመርጨት ስርዓት እንዲጀመር ምክንያት ሆነ፡፡ በወቅቱም ይህ አዲስና በጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ላይ ለውጥ ያመጣ አብይ ክስተት ነበር፡፡

በዚህ የውኃ ገንዳ የሚከወነው የጸበል መርጨት ስርዓትም እስከ አሁንም ይከወናል፡፡ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ጸበል የመርጨት ስርዓትን የሚመሩት ብፁዕ አቡነ ባስሊዮስ ሲሆኑ በዚህ አመትም ለመጀመሪያ ጊዜ በጃን ሜዳ ግቢ ውስጥ በሰራው ገንዳ አማካኝነት ለምዕመናኑ ጸበል የረጨት እሳቸው ናቸው፡፡

ከጣሊያን ወረራ በፊት የጥምቀት በዓል በስፋት ሽፋን በሚሰጠው በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በሚወጡ ጽሑፎች ላይ ስፍራውን "ጃን ሜዳ" በሚል ይገልጹት ነበር፡፡ ከጣሊያን ወረራ በኋላ መታተም የጀመረው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ደግሞ ስፍራውን "ጃንሆይ ሜዳ" በሚል ነበር የሚዘገበው፡፡ ይህም በስፍራው ስያሜ ላይ የመጣ አንዱ ለውጥ ነው፡፡

ይህ የስያሜ ለውጥ ስህተት እንደሆነ ደስታ (1962 ዓ.ም፣ 400) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤ ከ1933 ዓ.ም ወዲህ ግን አዲስ አበቦች 'ጃን ሆይ' ሜዳ ይሉታል፡፡ ስህተት ነው፤ ጃን ሆይ የቅርብ ስሚ ነውና፤ ዘርፍ አይሆንም፡፡ በማለት ሜዳው 'ጃን ሜዳ' እንጂ 'ጃን ሆይ ሜዳ' ተብሎ መጠራት የለበትም ይላሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ሜዳው ከ1933 ዓ.ም በፊት ይጠራበት በነበረው 'ጃን ሜዳ' በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡

ከጣሊያን ወረራ በኋላ መታተም በጀመረው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እስከ 1940 ዓ.ም ባወጣው እትሙ ድረስ የጥምቀት ማግስት ጥር 12፣ የሚከበረውን የቃና ዘገሊላ በዓልን ከኦሜድላ የድል ቀን ጋር በማገናኘት ሰፊ ሀይማኖታዊ ዘገባ ያቀርብ ነበር፡፡ ነገር ግን ከ1940 ዓ.ም ወዲህ በታተሙ የአዲስ ዘመን ጋዜጣዎች የጥምቀትና የቃና ዘገሊላ በዓላት ዜናዎች ላይ ይህ መሰል ዘገባ ማቅረብ አቁሟል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ይታተሙ ከነበሩ ጋዜጦች መካከል የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ (1949 ዓ.ም) የቃና ዘገሊላን በዓል ከኦሜድላ ድል ጋር አዛምዶ ዘግቧል፡፡



ፎቶ 3፡- የ1942 ዓ.ም ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ በጃን ሜዳ ተገኝተው የጥምቀት በዓልን ሲያከብሩ የሚያሳይ (ምንጭ፡ ታሪካዊ ፎቶግራፎች ከሚል የፌስቡክ ገጽ የተወሰደ)

አቡነ ባስልዮስ ጥር 6፣ 1943 ዓ.ም በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በተደረገ ስነስርዓት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሹመው ሲመጡ ለክብራቸው ሀያ አንድ መድፍ ተተኩሶ ነበር። በ1943 ዓ.ም የተከበረው የጥምቀት በዓል በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ የቅዳሴ ስነስርዓት መመራቱ በወቅቱ የተከሰተ አዲስ ሁነት ነው።

በጃን ሜዳ የጥምቀተ ባህሩ ማስፈጸሚያ ስፍራ በሚዘጋጀው ስፍራ በሰንደቅ ዓላማዎች አሸብርቆ፣ በሕዝብ ብዛት ደምቆ፣ በወታደር ሰልፍ አምሮ ይውላል። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም በየአመቱ ከመኳንቶቻቸው ጋር በስፍራው ይገኛሉ። በ1947 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አልጋወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋው ወሰንን፣ ልዑል መኰንን፣ መስፍነ ሐረር ልዑል ሣህለሥላሴን፣ ልዑል ራሳ ካሳን፣ ልዑል ራስ ስዩምን አስከትለው በሞተር ብስክሌተኞች ታጅበው በጥምቀተ ባህሩ ሲደርሱ ሴቱ በዕልልታ፣ ወንዱ በሆታ የደስታ ስሜት እየገለጸ ሲቀበላቸው፣ ተሰልፎ ይጠብቅ የነበረው ዘብ በብረት ንጉሳዊ ሰላምታ ማቅረቡን አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1947 ዓ.ም) ዘግቧል።

በዚህ አመት በተከበረው የጃን ሜዳ ጥምቀት ላይም የሥላሴ፣ የመድኃኒያለም፣ የማርያም፣ የበዓታ፣ የኢየሱስ፣ የዑራኤል፣ የዮሐንስ፣ የገብረኤል፣ የገብረመንፈስ ቅዱስ፣ የቅዱስ ሚካኤል እና የጊዮርጊስ ታቦታት በስፍራው እንደተገኙ ጋዜጣው ዘግቧል። የዚህ አመት የጥምቀት በዓልን የመሩትና ጥምቀቱን ያካሄዱት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ነበሩ። በ1949 ዓ.ም ደግሞ ከእነዚህ አስራ አንድ ታቦታት በተጨማሪ የኪዳነ ምሕረት ታቦት ተጨምሮበት በጥቅሉ አስራ ሁለት ታቦታት በጃን ሜዳ ማደራቸውን የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ (1949) ዘግቧል።

በ1952 ዓ.ም በተከበረው የከተራና የጥምቀት በዓልን አስመልክቶ "ለጧት ለማታ የንጉሠ ነገሥቱን ብሩህ ገጽ ለማየት የሚጓጓው የአዲስ አበባ ሕዝብ በዚህ በዓል ቀን የተወዳጅ ንጉሠ ነገሥት ብሩህ ገጽ ባለማየቱ በዓሉ ፍፁምነት አለው ሊባልና ግርማን የተጎናጸፈ ነበር ለማለት አልተቻለም።" በማለት አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1952፤1) ዘግቧል። ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ዓመት በጃን ሜዳ ያልተገኙት የጥምቀት ከተራ በዓልን በምጽዋ በማክበራቸው ነው። የምጽዋው የጥምቀት በዓል የተካሄደው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ የጃን ሜዳ ጥምቀት ደግሞ በብፁዕ አቡነ ማርቆስ ተካሂዷል።

አቡነ ባስልዮስ ሰኔ 21፣ 1951 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ ሆነው ተሾሙ። አጼ ኃይለ ስላሴም በበዓለ ሹመቱ ላይ ካይሮ ተገኝተው ነበር። ይህም የ1952 ዓ.ም የጃን ሜዳ ጥምቀት ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ የራሷን ፓትሪያርክ የሾመችበት ወቅት የተከበረ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል። ይህም በወቅቱ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ደስታ ፈጥሮ እንደነበር መረጃ ሰጪዎቹ ይገልጻሉ።[2]

---

[2] አቶ አዳነ ዳምጠው እና አስር አለቃ በርጋ ሞጆ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ የክብር ዘበኛ አባል የነበሩት መረጃ ሰጪዬ አስር አለቃ በርጋ ሞጆ የጥምቀት በዓል ሲከበር የንጉሱና የሕዝብ የልብስ ደንብ ምን ይመስል እንደነበር ሲገልጹ፡-

> የጃን ሜዳ ጥምቀት ሲከበር ንጉሡና መሳፍንቱ ይገኛሉ፡፡ እኔም የክብር ዘበኛ ወታደር ሆኜ አጅቤያቸዋለሁ፡፡ በቅርበትም አይቻቸዋለሁ፡፡ ንጉሱ በወታደራዊ ልብሳቸው ላይም ነጭ ካባ ይደርባሉ፡፡ ይህ የንጉሱ ካባ በወቅቱ መንጠልያ በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ ነጭ ቀለም ያለው ክብ የቡሽ ኮፍያም በብዛት ያደርጋሉ፡፡ የንጉሱ አልጋ ወራሽም የሙሉ ጄነራል ማዕረግን የሚያሳይ ሙሉ የወታደር ልብስ፣ በላዩ ላይ ደግሞ ነጭ ካባ አዘውትረው ይለብሳሉ፡፡ ልዑል ራስ ካሳ ለጥምቀት ጃን ሜዳ ሲገኙ አዘውትረው የሚለብሱት ጥቁር ካባ ነበር፡፡ ሌላው ሕዝብ ከጥጥ የተፈተለ እጀጠባብና ተነፋፈፍ ሴቱም እንደዚሁ ከጥጥ የተፈተለ ቡልኮ ቀሚስ ይለብሳል፡፡ ሴቶቹ ከጥራር የተሰራ ጃንጥላም ይይዛሉ፡፡ ያን ቀን ትልቅ ትንሹ ያለውን ልብስ ወንዝ ወርዶ በእንዶድ አጥቦ ንጹሕ ሆኖ ይውላል፡፡ በማለት ትውስታቸውን ይገልጻሉ፡፡

በወቅቱ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የቅርብ ጠባቂ የነበሩት የክብር ዘበኛ አባላት የራሳቸው የአለባበስ ስርዓት ነበራቸው፡፡ እነሱም የሚለብሱት እጀ ጉርድ ሸሚዝ፣ ገምባሌ፣ ቁምጣ፣ ጥቁር ቀበቶ፣ ጥቁር ጫማና ክብ ቡሽ ባርኔጣ ሲሆን በባርኔጣው በቀኝ በኩል አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ መሀሉ ላይ የአንበሳ ምስል ያለው ባንዲራ አለው፡፡ የክብር ዘበኛ አባላት በቡሹ ኮፍያ አናት ላይ እንዲሁም በግራና በቀኝ ትከሻቸው ላይ ወደ ታች የሚወርድ የአንበሳ ጎፈር አድርገው እንደማዕረጋቸው ቅደም ተከተል የንጉሱን ድንኳን ይጠብቃሉ፡፡[3]
በወቅቱ የክብር ዘበኛ ጦር በስድስት ሻለቃ የተቋቋመ ነበር፡፡[4] ተራ የደረሰው ሻለቃ በጥምቀት በዓል ወቅት በየአመቱ ልዩ ወታደራዊ ሰልፍ ያካሂዳል፡፡ በዕለቱም የክብር ዘበኛ አባላት ልዩ ልብሳቸውን ከነማዕረጋቸው በመልበስና ጠመንጃቸውን በትከሻቸው ላይ በማድረግ ንጉሱን ግራና ቀኝ በሰልፍ አጅበው ወደ ጃን ሜዳ ይሄዳሉ፡፡ በወቅቱ የክብር ዘበኛ አባል የነበሩት መረጃ ሰጪዬ አስር አለቃ በርጋ ሞጆ የተመደቡበት አራተኛ ሻለቃ ለሶስት ጊዜ ያህል ተራው ደርሶ ጃንሆይን ለጥምቀት በዓል ማጀቡን ያስታውሳሉ፡፡

> የክብር ዘበኛ አባላት በሰውነታችን አቋም ተመርጠን የምንገባ በመሆኑ አብዛኛዎቻችን ረጅምና ሰውነታችን ገዘፍ ያለ ስለነበር እኛ ለስራ ከተማ ውስጥ ስንቀሳቀስ ሕዝቡ ይፈራን ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የአዲስ አበባ ሕዝብ እኛ ክብር ዘበኞች ‘‘ጅሉ’’ በሚል ቅጽል ስም ይጠራን ነበር፡፡ ያን ግዜ፤- ‘‘የክብር ዘበኛ ከሆነ ባልሽ፣ ባትሞቺም ሞተሻል እግዜር ይማርሽ፡፡’’ የሚል ዘፈን ነበር፡፡

---

[3]አስር አለቃ በርጋ ሞጆ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡
[4] አስር አለቃ በርጋ ሞጆ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡

በማለት አስር አለቃ በርጋ ሞጆ ትውስታቸውን ይገልጻሉ። በወቅቱ ክብር ዘበኞችን “ጅሉ”፣ እንደሚባሉ ሁሉ፣ የጦር ሰራዊት “ባርያው” እንዲሁም የፖሊስ አባላት “ሌባው” በሚል ቅጽል ስም ይጠሩ እንደነበር መረጃ ሰጪዬ ያስታውሳሉ።[5]

በጃንሆይ ዘመን ለጥምቀት በዓል ከክብር ዘበኛ፣ ከፖሊስ፣ ከጦር ሰራዊትና በከተማ ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ፈረሰኞች ተመርጠው የፈረስ ግልቢያና የፈረስ ጉግስ በጃን ሜዳ ይጫወታሉ። በዕለቱም ከፈረስ ጉግስ በተጨማሪ የገና ጨዋታ በቡድን በቡድን በመሆን ይጫወታሉ። ቡድኖቹም ከተለያዩ የጦር ክፍሎችና ከከተማው ነዋሪዎች የተመረጡ ናቸው። የገና ጨዋታው በሁለት መንገድ ይካሄዳል። አንደኛው በእግር በመሮጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በፈረስ ላይ በመሆን የሚጫወቱት ነው። በእለቱ የገና ጨዋታን በእግርና በፈረስ የሚጫወቱ ሲሆን ተጋጣሚዎቹም በቡድን ተለይተው ይጫወታሉ። ጨዋታውን የሚያስጀምሩት የአዲስ አበባ ከንቲባ ናቸው።[6]

ከጥምቀተ ባህሩ ወደ ቤተክርስቲያናት የሚሄዱ ታቦታት በአንድ ላይ በምዕመናን እልልታና ጭፈራ እንዲሁም በካህናት ዝማሬ ታጅበው ከጃን ሜዳ ጉዞ ይጀምራሉ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና መኳንንት ታቦታትን ከኋላ አጅበው ይሄዳሉ። ታቦታቱ የካቲት 12 መታሰቢያ አደባባይ ጋር ሲደርሱ የማሳረጊያ ጸሎት ይጸለይና የተወሰነ እረፍት ያደርጋሉ።[7] ወደ አራት ኪሎ፣ ወደ ስድስት ኪሎ፣ ወደ ፒያሳ፣ ወደ ቀጨኔ መስመር የሚሄዱ ታቦታትም ስንብት ያደርጋሉ። ታቦታቱ ሲሰናበቱም ታቦተ ህጉን የተሸከሙ ካህናት ፊት ለፊት ይቆሙና ሶስት ጊዜ ከእግራቸው ወደ መሬት ሸብረክ በማለት ነው።[8]


የጥምቀት በዓል በጃንሆይ ሜዳ ሲከበር።

ፎቶ 4፡- የ1948 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ሲከበር የሚያሳይ (ምንጭ፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 1948 ዓ.ም)

[5] አቶ መድህን ይሁነኝ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 2006 ዓ.ም. አዲስ አበባ።
[6] አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣የካቲት፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[7] አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[8] መርጌታ ማስረሻ ወንድሙ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

ጃንሆይ የቅዱስ ማርቆስን ታቦት አስገብተው ከግቢው በኋላ በኩል ባለው መውጫ ወደ ቤተ መንግስታቸው ይገባሉ።[9] እሳቸው ቤተመንግስታቸውን ከገነተ ልዑል ወደ ኢዩቤልዩ ካዘዋወሩ በኋላ የመድኃኔዓለምን (መንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል) ታቦት መሸኘት ጀመሩ። በማግስቱ በጃን ሜዳ ተገኝተው የየካ ሚካኤልን ታቦት ያስገባሉ።[10]

በታህሳስ 4 ቀን 1953 ዓ.ም በአቶ ግርማሜ ነዋይ፣ በብርጋዴል ጄኔራል መንግስቱ ነዋይና በሌትራል ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ አማካኝነት የክብር ዘበኛ አባላት መፈንቅለ መንግስት ሙከራ አካሄዱ። በጦር ሰራዊትና በስሩ የሚገኙ የምድር ጦር ሰራዊት፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ፣ የአየር ኃይል ሰራዊት እንዲሁም የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባላት ባካሄዱት ዘውዱን የመጠበቅና ለንጉሱ ያላቸውን ታማኝነት ለመግለጽ ባካሄዱት የመከላከል እርምጃ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራው ከሸፈ (ታደሰ፣ 2004 ዓ.ም)።

የክብር ዘበኛ አባል የነበሩት መረጃ ሰጪዬ አስር አለቃ በርጋ ሞጆ በዕለቱ የተፈጸመውን ሁኔታ እንዲህ ይገልጻሉ። "ያን ቀን ሲነጋ ሲል በአለቃችን አማካኝነት ተጠንቀቁ የሚል ትዕዛዝ ተሰጠን እነሱም በግልጽ የነገሩን ነገር የለም። መጨረሻ ላይ ሰልፍ ካካሄድን በኋላ ጦር ሰራዊት የንጉሱን ዘውድ ሊገለብጥ ስለሆነ ለዘውዱ ክብር፣ ለሀገርና ለኃይማኖታችሁ ስትሉ በርትታችሁ ተዋጉ የሚል ትዕዛዝ ተሰጠን። ተሰልፈን ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር (በተለምዶ መሿለኪያ አካባቢ የሚገኘው) መጓዝ ስንጀምር ጦርነት ተጀመረ። በአየር ወረቀት ተበተነ። በወቅቱም ጳጳሱ አቡነ ባስልዮስ ወረቀት በትነው ነበር። ጓደኛዬ ወረቀቱን አንብቦ ‹‹እኛ ነን እንዴ ያመጽነው? ብሎ ጠየቀኝ። የተበተነውንም ጽሑፍ አነበበልኝ ወዲያው ደንግጬ ከነመሳሪያዬ ቤቴ ገብቼ ተደበኩኝ። የጃንሆይ አዋጅ ሲነገር ሄጄ እጅ ሰጠው።" በማለት ስለ መፈንቅለ መንግስቱ ታሪክ አጫውተውኛል።[11]

መፈንቅለ መንግስቱ ከከሸፈ በኋላ ተሳታፊ የነበሩት የክብር ዘበኛ አባላት በጦር ሰራዊት፣ በፖሊስና በፈጥኖ ደራሽ አባላት ከያሉበት እየተለቀሙ ሲገደሉና ሲታሰሩ ቆዩ። በሕይወት የተረፉትም የክብር ዘበኛ አባላት መሳሪያቸውን እንዲያስረክቡና ለመንግስት እጅ እንዲሰጡ አዋጅ ተነገረ። አባላቱም በአዋጁ መሰረት ለመንግስት እጅ ሰጥተው እስር ቤት ገቡ።

ጃንሆይም "ወታደር ታዛዥ ነው፣ እነሱ ምን አደርጉ፣ አለቆቻቸው ያዘዟቸውን ነው የፈጸሙት።" በማለት አብዛኛዎቹን የክብር ዘበኛ አባላት ምህረት አድርገውላቸው፤ በኤርትራ፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በባሌ፣ በትግራይና በሌሎች ቦታዎች በጦር ሰራዊት ስር ተበታትነው እንዲሰሩ ተመደቡ።[12] መረጃ ሰጪዬ አስር አለቃ በርጋ ሞጆም ከእስር ተለቀው በጦር ሰራዊት ስር ነጌሌ ቦረና ተመድበው ስራ ጀመሩ።

---

[9] አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[10] አቶ ይበልጣል ማርዬ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[11] አስር አለቃ በርጋ ሞጆ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[12]አስር አለቃ በርጋ ሞጆ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

ከታህሳስ ግርግር በኋላ፤ በዚሁ ዓመት በጥምቀት በዓል ላይ ጃንሆይን ያጅቧቸው የነበሩ የክብር ዘበኛ አባላት በግርግሩ ምክንያት በመበተናቸው በጦር ሰራዊትና በፖሊስ አባላት ተተኩ። በዚህ ምክንያት በ1953 ዓ.ም የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል የክብር ዘበኛ ሰራዊት ከተቋቋመ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ንጉሱ በክብር ዘበኛ ጦር ሰራዊት አባላት ሳይታጀቡ ያከበሩት በዓል ነው። የክብር ዘበኛ ጦር ድጋሚ እስከሚቋቋም ድረስም ጃንሆይ በጦር ሰራዊትና በፖሊስ አባላት ይታጀቡ ነበር። በታህሳሱ ግርግር ታላላቅ የመንግስት ባለስልጣናት፣ አርበኞችና መኳንንት በመገደላቸው ምክንያት ህዝቡ ሀዘኑን ለመግለጽ በዚህ ዓመት የተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ የነበረው ባህላዊ ሙዚቃ፣ ሆታና ጭፈራ እንደቀድሞው እምብዛም ያልደመቀ እንደነበር መረጃ ሰጪዎቹ ያስታውሳሉ።[13]

በ1954 ዓ.ም የጥምቀት በዓልን አንድ የሻምበል የክብር ዘብ በጃን ሜዳ ተገኝቶ የግርማዊነታቸው ዙፋን በተዘረጋበት ታላቅ ድንኳን እስከ ባሕረ ጥምቀቱ ባለው ስፍራ ግራና ቀኝ በብረት ተሰልፎ ጃንሆይን በክብር እንደተቀበለ አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1954 ዓ.ም) ዘግቧል። በዚህ አመትም ንጉሱ ለጥምቀት በዓል በክብር ዘብ ድጋሚ መታጀባቸውን ያሳያል።

በ1955 ዓ.ም ንጉሱ የጥምቀት በዓልን ያከበሩት በአስመራ ከተማ ነው። (አዲስ ዘመን፣ 1955 ዓ.ም)። ንጉሱም አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን እና የተቀሩትን የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው በሞተር ብስክሌተኞች ታጅበው በአስመራ የጥምቀት በዓል ማክበሪያ ስፍራ ተገኝተው አክብረዋል። ይህ አመት ንጉሱ አስመራ በመሄዳቸው ምክንያት ጃን ሜዳ ያልተገኙበት የጥምቀት በዓል መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። የዚህ አመት የአዲስ አበባ ጃን ሜዳ ጥምቀት በዓል ጸሎተ ቡራኬ ያደረጉት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ናቸው።

በ1956 ዓ.ም በተፈሪ መኮንን እና በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማካኝነት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስትያን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የ"ተምሮ ማስተማር" ማህበር ተቋቋመ (እደ ማርያም፣ 2006 ዓ.ም)። በተምሮ ማስተማር ማህበር አባላት አማካኝነት የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል አከባበር ስርዓት ልዩ ድምቀት መፍጠር ጀመረ። በወቅቱ የተምሮ ማስተማር ተማሪዎችም በጥምቀት በዓል ላይ ልዩ ልዩ መዝሙሮችን በማቅረብ፣ የተለያዩ ድራማዎችን በማሳየት፣ አንድ አይነት ልብስ ለብሰው ታቦታትን ማጀብ፣ በጃን ሜዳ ግቢ ውስጥ ከእንጨት በተሰራ ማማ ላይ በመሆን ለህዝቡ መንፈሳዊ ትምህርት ማስተማርና በአማረ ሰልፍ መዝሙር ማቅረብ ጀመሩ።[14]

የተምሮ ማስተማር ተማሪዎችም የተለያዩ የመልአክትና የቅዱሳን ስዕላት፣ የጥምቀት በዓልን የሚያሳዩ ስዕላት በጨርቅ ላይ በመሳል እንዲሁም አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለም ያላቸው ጨርቆችን በመቀጣጠል በገመድ በማሰር ረጃጅ እንጨቶችን በመትከል ስፍራውን ያደምቁት ነበር። ከእነዚህ መንፈሳዊ ተማሪዎች

---

[13]አቶ አዳነ ዳምጠው እና አቶ ይበልጣል ማርዬ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[14]አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

በተጨማሪ አዝማሪዎች በመሰንቆ የተለያዩ ዘፈኖችን በመዝፈን በዓሉን ያደምቁት እንደነበር መረጃ ሰጪዬ ያስታውሳሉ፡፡[15]

ንጉሱ ለጥምቀት ወደ ጃን ሜዳ ሲመጡ አዘውትረው ቡላ መልክ ያለው የወታደር ልብስ ከእነማዕረጉ ይለብሳሉ፡፡ ንጉሱ የሚለብሱት የመታደር ልብስ በወቅቱ ገበርዲን በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ ንጉሱ በወታደራዊ ልብሳቸው ላይ የማርሻል የማዕረግ ደረጃን የሚያሳዩ ምልክቶች ያደርጋሉ፡፡ አፄ ኃይለ ስላሴ የማርሻል ማዕረግ ማድረግ የጀመሩት በጥር 24 ቀን 1957 ዓ.ም የእንግሊዝ ንግስት ኤልሳቤት ከባለቤታቸው ፊሊፕ ጋር ኢትዮጵያን ለመጎብኘት በመጡበት ወቅት የጦር ሰራዊት ማርሻል ማዕረግ በንግስት ኤልሳቤት አማካኝነት ከእንግሊዝ መንግስት ከተበረከተላቸው በኋላ ነው (ዘሪሁን፣1993 ዓ.ም)፡፡

በ1957 ዓ.ም የተከበረው የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ከመቼውም በላይ ደማቅ እንደነበር አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1957 ዓ.ም) ገልጿል፡፡ በዕለቱም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፣ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ላይ ተካፋይ ለመሆን የመጡ ብጹዓን ወቅዱሳን ፓትርያርኮች በተገኙበት የጥምቀት በዓል በደማቅ ስርዓት ተከብሯል፡፡

በ1957 ዓ.ም በጃን ሜዳ በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ የተገኙት፣ የእስክንድሪያ ፓትርያርክ ፖፕ የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ብጹዕ ቅዱስ አባ ቁርሎስ 6ኛ፣ የሶርያ ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ ሞራንማር አግናጢዮስ ያዕቆብ ሳልሳዊ፣ የአርመንያ ፓትርያርክ ኮን ቀዳማዊ፣ የህንድና የሶርያ ፓትርያርክ ናማር ባስሊዮስ ቀዳማዊ፣ የኪልት ፓትርያርክ ኩሬንማዊ ይገኙበታል፡፡ ብጹዓን ወቅዱሳን ፓትርያርኮቹ በተገኙበት የ1957 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ሲከበር በኢትዮጵያ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የመጀመሪያው ነው፡፡

በ1959 ዓ.ም ንጉሱ የጥምቀት በዓልን ያከበሩት በኤርትራ ነው፡፡ (አዲስ ዘመን፣ 1959 ዓ.ም)፡፡ ንጉሱ የጥምቀት በዓልን አስመራ አክብረው በማግስቱ የቃና ዘገሊላ በዓልን በምጽዋ በመገኘት በመርሶ አህማር (የመርከበኞች ወደብ) በሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተገኝተው ማክበራቸውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1959 ዓ.ም) ዘግቧል፡፡ በዚህ አመት በተከበረው የጃን ሜዳ ጥምቀት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ጸሐፊ አክሊሉ ሀብተወልድ እና ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በተገኙበት ተከብሯል (አዲስ ዘመን፣ 1959 ዓ.ም)፡፡ ንጉሱ የ1952 ዓ.ም፣ የ1955 ዓ.ም እና የ1959 ዓ.ም የጥምቀት በዓልን በኤርትራ ያከበሩበት ምክንያት ከኮንፌዴሬሽኑ መፍረስ ጋር በተያያዘ የዲፕሎማሲና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ስራ አንዱ አካል ነበር፡፡

በ1960 ዓ.ም በጥምቀት በዓል ላይ በተነሳ የእርስ በርስ ጠብ ምክንያት ስምንት ሰዎች መቁሰላቸውን ኮሎኔል ትርፌ ይመኑ መግለጻቸውን የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ (1960 ዓ.ም) ዘግቧል፡፡ የጋዜጣው ሪፖርተር የጠቡ መነሻ ምክንያት በሁለት ቡድኖች ልዩ ልዩ ዜማዎች ሲያሰሙ የነበሩት ተጨዋቾች በግጥም ሽሚያና በከበሮ

[15]አቶ ይስማው አየለ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡

ጩኸት የተነሳ እንሆነ ገልጿል፡፡ መረጃ ሰጪዬ አቶ አዳነ "በጥምቀት በዓል ወቅት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጠብ ውስጥ መግባታቸው የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የ1960 ዓ.ም የጃን ሜዳ ግጭት በአሁኑ ዘመን አጠራር የብሔር ግጭት አይነት ነው፡፡ ሁለት የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች በቡድን ተለያይተው ነው የተደባደቡት" በማለት በወቅቱ የተነሳውን ጠብ ይገልጻሉ፡፡[16]

በጃንሆይ ዘመን ከሕዝቡ በተጨማሪ አንበሶችም ለጥምቀት በዓል ልዩ ድምቀት ይሰጡ ነበር፡፡ በዘመኑ ሞላ በሚል ስያሜ የሚታወቅ አንበሳ ዝነኛ ነበር፡፡ ሞላ በሕዝባዊ በዓላት ላይ በመገኘት ለበዓላት ድምቀት ይፈጥር እንደነበር ይነገራል፡፡ ሞላ፣ ከደቡብ ኦሞ ከበና ጫካ፣ በአሁኑ አጠራር ከማጎ ብሔራዊ ፓርክ የመጣ ደቦል ነው፡፡ አንበሳው ሞላ የሚለውን ስያሜ ያገኘው በማጎ ፓርክ ውስጥ ሞላ ከሚባል ስፍራ በመምጣቱ ነው፡፡

ሞላ በአጼ ምኒልክ ትዕዛዝ የመጣ የአንበሳ ደቦል ነው፡፡ ሞላን ከበና ጫካ ይዘው በመምጣት ለንጉሱ በስጦታ ያስረከቡት አባታቸው ባላምባራስ ዶሪ ወንኪ መሆናቸውን ፊታውራሪ መኮንን ዶሪ ይገልጻሉ፡፡[17] በወቅቱ ሞላ የተባለው አንበሳ ሚስቱን በክርኑ መትቶ ገድሏል እየተባለ በስፋት ይወራ እንደነበር መስማታቸውን መረጃ ሰጪዩ ያስታውሳሉ፡፡[18]




ፎቶ 5፡- የ1961 ዓ.ም ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ በጃን ሜዳ ተገኝተው የጥምቀት በዓልን ሲያከብሩ የሚያሳይ (ምንጭ፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 1961 ዓ.ም)

በ1961 ዓ.ም የጦር ሰራዊት ቴክኒክ ክፍል (በአሁኑ አጠራር በተለምዶ ሲግናል ተብሎ ይጠራል) ወንድና ሴት አንበሶችን በብረትና በቃጫ ክር ሰርተው ለጥምቀት

[16]አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡
[17]ፊታውራሪ መኮንን ዶሪ፣ ቃለ መጠይቅ፣ አሻም ቴሌቪዥን፣ አናርጅ እናውጋ፣ የእኛ ወርቆች ፕሮግራም፣ ጥቅምት፣ 2012 ዓ.ም፡፡
[18]አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡

በዓል በክፍት መኪና ታቦታትን እንዲያጅቡ አድርገዋል፡፡[19] ከቃጫ ክር የተሰሩት አንበሶችም ከትክክለኛ አንበሳ የተቀዳ ድምጽ እንዲያወጡ ተደርጓል፡፡

የቃጫ አንበሶቹ ያሉበት መኪና ላይ ወደ ላይ የሚወጣና ወደ ታች የሚወርድ ሊፍት መሰል ማሽን ነበረው፡፡ ኦፕሬተሩ ከመኪናው ውስጥ ሆኖ ማሽኑን ጫን ሲለው መጀመሪያ ወንዱ የቃጫ አንበሳ ከወገቡ በላይ ይወጣና ያገሳል፡፡ ቀጥሎም ወንዱ የቃጫ አንበሳ ዝቅ ይልና ሴቷ የቃጫ አንበሳ ከወገቧ በላይ ትወጣና ታገሳለች፡፡[20] በዚህ መልኩ ተራ በተራ እየወጡ በማግሳት ለበዓሉ ታላቅ ድምቀት ፈጥረው እንደነበር በወቅቱ የጦር ሰራዊት የቴክኒክ ክፍል የመገናኛ ሬዲዮ ባለሙያ የነበሩት መረጃ ሰጪዬ አቶ አዳነ ዳምጠው ያስታውሳሉ፡፡

በዚህ ወቅት ህዝቡ ትክክለኛ የተፈጥሮው አንበሳ እንደሆነ እንጂ ከቃጫ ክር የተሰራ አንበሳ እንደሆነ አያውቅም ነበር፡፡ ከሞላና ከጦር ሰራዊት ቴክኒክ ክፍል የቃጫ አንበሶች ቀጥሎ መኩሪያ በሚል ስያሜ የሚታወቅ የክብር ዘበኛ አንበሳ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት ድረስ ለጥምቀት በዓል ጃን ሜዳ በመገኘት ታቦታትን ያጅብ ነበር፡፡[21] በ1945 ዓ.ም የክብር ዘበኛ አባል የሆኑት ሀምሳ አለቃ ገብሬ አበበ፣ መኩሪያን ተረክበው ማሳደግ እንደጀመሩ፣ ልጃቸው አቶ ሀብታሙ ገብሬ ገልጿል፡፡[22] አንበሳው፤ መኩሪያ የሚለውን ስያሜ ያገኘው የመጀመሪያው የክብር ዘበኛ አዛዥ በነበሩት በመኩሪያ ባንተይርጉ ስም ነው፡፡

የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አባ ጁስቲንያን በ1961 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት የጥምቀት በዓልን በጃን ሜዳ በመገኘት አክብረዋል (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ 2000 ዓ.ም)፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አባ ጁስቲንያን ባሕረ ጥምቀቱን ባርከው ጸበሉን በመርጨት በዓሉን ማስጀመራቸውን እንዲሁም ያደረጉትን ንግግር አስመልክቶ አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1961 ዓ.ም) ዘገባ ሰርቷል፡፡

በ1962 ዓ.ም በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ የዴንማርክ ንጉሥ ግርማዊ ፍሬዴሬክና ንግሥት ኢንግሪድ በጃን ሜዳ ከአጼ ኃይለሥላሴ ጋር በመገኘት በዓሉን አክብረዋል፡፡ በዚሁ አመትም በተከበረው የጥምቀት በዓል ወቅት በደረሰ የትራፍሪክ አደጋ ስድስት ሰዎች መሞታቸውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1962 ዓ.ም) ዘግቧል፡፡

የጥምቀት በዓል በጃን ሜዳ ሲከበር በስፍራው የአልኮል መጠጥ፣ ምግብ፣ ለስላሳ መጠጥ ሁሉም ይሸጥ ስለነበር መጠጥ ጠጥቶ እርስ በርስ መጣላት የተለመደ እንደነበር መረጃ ሰጪዬ ይገልጻሉ፡፡[23] ነገር ግን በ1962 ዓ.ም በጥምቀት በዓል የማክበሪያ ስፍራ በሆነው ጃን ሜዳ ላይ በበዓሉ ወቅት የአልኮል መጠጥ መሸጥ መከልከሉን አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1962 ዓ.ም) ዘግቧል፡፡ በ1963 ዓ.ም በድሬደዋ

[19] አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡
[20] አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡
[21] አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡
[22] አቶ ሀብታሙ ገብሬ፣ ቃለመጠይቅ፣ በኢቲቪ መዝናኛ ፍለጋ ፕሮግራም፣ ጥር 2011 ዓ.ም፡፡
[23]አቶ ይስማው አየለ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፡፡

በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ሴቶችን የቆነጠጡ አንድ መቶ ሀያ ሁለት ልጆች በፖሊስ ተይዘው መታሰራቸውን አዲስ ዘመን (1963 ዓ.ም) ዘግቧል፡፡ ይህ ዜና በጥምቀት ላይ ይቀርቡ ከነበሩና የተለመዱ ከሆኑ የበዓል የደስታ መግለጫ የጋዜጣ ዘገባዎች በይዘቱ የተለየ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡



ፎቶ 6፡- የ1965 ዓ.ም የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ዡርዥ ፓምፒዱ እና ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል ሲያከብሩ የሚያሳይ (ምንጭ፡ ታሪካዊ ፎቶግራፎች ከሚል የፌስቡክ ገጽ የተወሰደ)

በ1965 ዓ.ም የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ዡርዥ ፓምፒዱ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግብዣ ኢትዮጵያን ለሶስት ቀን ለመጎብኘት አዲስ አበባ በገቡበት ወቅት በጃን ሜዳ በመገኘት የጥምቀት በዓልን አክብረዋል፡፡ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የሀይማኖት መሪዎችና ታላላቅ ሰዎች በበዓሉ ላይ መገኘታቸው በወቅቱ የጥምቀት በዓል ለዲፕሎማሲና ለሀገር ገጽታ ግንባታ የነበረው ሚና ከፍተኛ እንደነበር ያሳያል፡፡

የጃን ሜዳን የጥምቀት በዓል ላይ የሚከወነውን ስርዓተ ቅዳሴና መዝሙር የሚያቀርቡት በየአመቱ ተራ የደረሰው ደብር ነው፡፡ በየወቅቱ ተራ የደርሷቸውን ደብሮች አዲስ ዘመን ጋዜጣ በየአመቱ ዘግቧቸዋል፡፡ በ1955 ዓ.ም የመንበረ መንግስት ቅዱስ ገብረኤል፣ የደብረ ሰላም መድኃኒያለም እና የደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ካህናትና መዘምራን በአንድ ላይ፣ በ1956 ዓ.ም የደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል መዘምራን፣ 1959 ዓ.ም የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መዘምራን እንዲሁም በ1960 ዓ.ም የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ደብር መዘምራን ተረኛ የበዓሉ አዘጋጆች እንደነበሩ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች የጥምቀትን በዓልን ለማክበር በርካታ ታቦታት ወደ ጃን ሜዳ ይመጡ ነበር፡፡ ከእነዚህ ታቦታት መካከል የተወሰኑት ጃን ሜዳ ድረስ ረጅም ርቀት ይጓዙ ነበር፡፡ ይህን ወደ ጃን ሜዳ የሚደረገውን ረጅም ጉዞ ለማስቀረት እንደ አቅራቢያው በተዘጋጁ ቦታዎች ጥምቀትን እንዲውሉ በ1965 ዓ.ም መወሰኑን አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1965 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡ ከዚህን ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ ታቦታት ጃን ሜዳ ቀርተው በየአቅራቢያው በሚገኝ ስፍራ ጥምቀትን

ማክበር ጀመሩ። በጃን ሜዳ አቅራቢያ የሚገኙ ታቦታትም በተለመደው መልኩ በስፍራው ለጥምቀት መውጣት ቀጥለዋል።

በ1966 ዓ.ም የመላው ራሺያ ፓትሪያርክ አቡነ ፒሚቶ ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት የጥምቀት በዓልን በጃን ሜዳ በመገኘት አክብረዋል (አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 1966 ዓ.ም)። አቡነ ፒሚቶ ባሕረ ጥምቀቱን ባርከው ጸበሉን በመርጨት በዓሉን ማስጀመራቸውን እንዲሁም ያደረጉትን ንግግር አስመልክቶ አዲስ ዘመን ጋዜጣ (1966 ዓ.ም) ዘገባ ሰርቷል።

## 8- የጥምቀት በዓል እንደ ልዩ ማህበራዊ መድረክ፤ በጃን ሜዳ

የጃን ሜዳ ጥምቀት ከኃይማኖታዊ ስርዓትነቱ በተጨማሪ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች መከወኛ ነው። ከእነዚህ ማህበራዊ ጉዳዮች መካከል በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት የአቤቱታ ማቅረቢያ መድረክ ነበር። በጥምቀት በዓል ላይ ለንጉሱ አቤቱታ ካቀረቡት አካላት መካከል የጉራጌ ማህበረሰብ አንዱ ነው። በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ ዕቃ የሚሸከሙ ግለሰቦችን "ጉራጌ … ጉራጌ" በሚል መጥራት የተለመደ ነበር። ይህ ልምድ እንዲቆም በአዲስ አበባና አካባቢው የሚኖሩ የጉራጌ ማህበረሰብ ተወላጆች ተሰባስበው ለጃንሆይ አቤት ለማለት ተዘጋጁ (መሐመድ፣ 2005 ዓ.ም)።

ጃንሆይ በየካ የሚገኘውን የሚካኤል ታቦት አስገብተው ወደ ቤተመንግስታቸው ሲመለሱ፣ ሁሉም የጉራጌ ተወላጆች ልጡ የተላጠ ረጃጅም የባህር ዛፍ ሽመል ይዘው፣ በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፉ። ጃንሆይም ሁኔታውን ሲጠይቁ አቤቱታ መሆኑን ተረዱ። አቤቱታውም "ተሸካሚ ጉራጌ እየተባለ መጠራት የለበትም፣ ይህን ይስቀሩልን።" የሚል ነበር። ጃንሆይም አቤቱታውን ሰምተው ተሸካሚ ሲጠራ የሚችልባቸው አማራጭ ስሞች እንዲፈለጉ አደረጉ። በወቅቱ የቀረቡት አምስት አማራጭ ስሞች ሀማል፣ ኩሊ፣ ባቱ፣ ተሸካሚ እና ሰርቶ በሌ ነበሩ። ከእነዚህ መካከል "ኩሊ" የሚለው ስም ተመረጠ (መሐመድ፣2005 ዓ.ም)።

ታቦተ ህጉን ለማጀብ ወደ ጃን ሜዳ የሚመጣው ሕዝብ እንደ ባህሉ የተለያዩ አልባሳትን ይለብሳል። ሕዝቡም "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ።" የሚል ምሳሌያዊ አነጋር አለው። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገርም ለጥምቀት ከሆነ አዲስ ልብስ ይህ ካልሆነም ካለው ልብስ መካከል የተሻለ ውበት ያለውን አጥቦ ይለብሳል። ለጥምቀት በዓል ወንዱ በነጭ የባህል ልብስ፣ ተፈሪ ልብስ፣ ተነፋነፍ፣ ባተሁለት በመልበስ ይዋባል። ሴቶች በነጭ ጥበባቸው ላይ መልጎም በመባል የሚጠራ የብር ጌጥ በማድረግ፣ ጸጉራቸውን በተለያየ አይነት የጸጉር ስራ በመሰራትና ጥሩ ጠረን ያላቸውን ቅጠላ ቅጠል ወይም ሽቶ በመቀባት ውብ ሆነው ወደ ጃን ሜዳ ይሄዳሉ።[24]

---

[24]አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

የጥምቀት በዓል ከሀይማኖታዊ እሴቱ በተጨማሪ የተለያዩ ብሔረሰቦች ያላቸውን የጭፈራና የዘፈን ባህል የሚያሳዩበት እንዲሁም ወንድና ሴት ወጣቶች ለትዳር የሚሆናቸውን ሰው የሚተዋወቁበትና የሚያጩበት ስፍራ በመሆኑ ልዩ ስፍራ የሚሰጠው ነው። በወቅቱም ወንዱ ለትዳር ትሆነኛለች የሚላትን ልጃገረድ ሎሚ በመወርወር አካሏን ወይም የያዘችውን ጥላ ይመታል። ልጅቷም ልጁን ለመተዋወቅ ፍቃደኛ ከሆነች የመሽኮርመም ምልክት ታሳያለች። በዚህ መልክ ወጣቶች እርስ በርስ ይተዋወቁና ትዳር ይመሰርቱ ነበር።

በወቅቱ አንድ ወጣት ለትዳር የሚፈልጋትን ልጃገረድ ለመተዋወቅ ሎሚ ከመወርወር በተጨማሪ ሜታ ከረሜላ፣ ቸኮሌት ከረሜላና ማስቲካ ተወዳጅ የነበሩ በመሆናቸው ገዝቶ ይሰጣት ነበር።[25] በጃን ሜዳ የሎሚ ውርወራ ሳቢያ ተጫጭተው ለወግ መዓረግ የበቁ በርካታ ግለሰቦች አሉ። ልጃገረዶች ከቤት የመውጣት፣ ከወንድ ጋር የመተዋወቅ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር የመገናኘት እንዲሁም ውብ ሆነው የመታየት እድል የሚያገኙት በጥምቀት በዓል በመሆኑ ከሌላው ቀን በተሻለ በእለቱ ነጻነት የሚያገኙበት ነው።

የጥምቀት በዓል ከእነዚህ ባህላዊ ክንዋኔዎች በተጨማሪ የተጣሉ ሰዎች ይቅርታ የሚጠያየቁበትና የሚታረቁበት የ"እርቅ" በዓል ነበር።[26] የጥምቀት በዓል ከእርቅ በዓልነቱ በተጨማሪም ወጣት ወንድና ሴት ልጆች፣ የቤት ሰራተኞች፣ ለትዳር የደረሱ ጎረምሶችና ልጃገረዶች አምረውና ደምቀው ከቤት በመውጣት ውጭ የሚውሉበትና የሚያመሹበት በዓል ነው። በዕለቱም ቤተሰቦች በልጆቻቸው ላይ የሚያደርጉትን ቁጥጥር የሚተውቡት ነው። ይህ በመሆኑ የጥምቀት በዓልን የ‹‹ነጻነት›› ቀን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

*ማጠቃለያ*

ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በጃን ሜዳ የጥምቀት በዓል የአከባባር ስርዓቶች የነበራቸውን ታሪክ የሚያሳየው ይህ ጥናት "ኦራላይዝድ ሂስትሪ" የንድፈ ሃሳብ መንገድን የተከተለ ነው። በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረትም በጥምቀት በዓል ላይ በጃን ሜዳ፣ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶችን በጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። ለጥናቱም ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ ቀርበዋል።

ይህ ጥናት ትኩረት ካደረገበት ከ1917 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ የጥምቀት በዓል በጃን ሜዳ ያለማቋረጥ መከበሩን ጥናቱ አሳይቷል። በኢትዮጵያ የተከሰቱ አበይት የታሪክ አጋጣዎች በስፍራው በተከበሩ የጥምቀት በዓላት ላይ ላይ አዳዲስ ሁነቶች እንዲከሰቱ ምክንያት እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። የጥምቀት በዓል ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ባሉት አመታት በንጉስ አጀብ፣ የወታደር ትርኢት፣ የካህናት፣ የሕዝብ አጀብ በደማቅ ሁኔታ ይከበር እንደነበር ጥናቱ አሳይቷል። በበዓሉ

[25]አቶ አዳነ ዳምጠው፣ ቃለ መጠይቅ፣ጥር፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።
[26]ሻለቃ መንግስትዓብ ይደጉ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 2006 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ሁነቶች በየወቅቱ የነበረውን የዘመን መንፈስ እንደሚያሳዩ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን በጥምቀት በዓል ወቅት የነበረው የንጉስ አጀብ፣ ዘፈን፣ ጭፈራና ሆታ እጅግ ደማቅ ነበር፡፡ ታቦተ ህጉን ከዘማሪ ካህናት በተጨማሪ አዝማሪዎች፣ የተምሮ ማስተማር ተማሪዎችና አንበሶች ያጅቡ ነበር፡፡ የጥምቀት በዓል አከባበር በጋዜጣ ሰፊ ሽፋን ይሠጠው ነበር፡፡ በጃን ሜዳ በሚከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ከተለያዩ አለማት የመጡ የኃይማኖት አባቶች፣ ኮርዶፕሎማቶች፣ አምባሳደሮችና የሀገራት መሪዎች ይገኙ ነበር፡፡ ይህም የጥምቀት በዓል ለዲፕሎማሲ፣ ለሕዝብ ለሕዝብ ትስስርና ለሀገር ገጽታ ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከ1917 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ባሉት አመታት ከተከበሩ የጥምቀት በዓላትም በአገሪቷ የነበረውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ስነምግባራዊ ጉዳዮች የሚገልጹ በርካታ አዳዲስ ሁነቶች እንደተከሰቱ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

መሐመድ ደርባቸው፡፡2005፡፡ ደንዲ የግዞት አምባ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፡፡2002፡፡ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት (1896-1922)፡፡ አአዩ ፕሬስ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ሥርግው ሐብለሥላሴ፡፡1983፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ የአዲሱ ስልጣኔ መስራች፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ሰሎሞን ተሾመ፡፡2007፡፡ ፎክሎር ምንነቱ እና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡2013፡፡ "የጥምቀት በዓል አከባበር ከአይሂዳ እስከ ጃን ሜዳ (ከ34 ዓ.ም - 1966 ዓ.ም)፡፡" *ታዛ መጽሔት ቅጽ፣ 04 ቁጥር 41*፣ የካቲት 2013 ዓ.ም ዕትም፡፡ ገጽ፤ 10-14)፡፡

ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ፡፡1917፡፡ ጥር 14፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡ በኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1918፡፡ ጥር 17፣ 2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡ በኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1919፡፡ ጥር 15፣ 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡ በኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1921፡፡ ጥር 16፣ 5ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1922፡፡ ጥር 15፣ 6ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1923፡፡ ጥር 14፣ 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1924፡፡ ጥር 19፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፡፡ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

———————፡፡1925፡፡ ጥር 18፣ 9ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፡፡ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

———————::1926:: ጥር 17፣ 10ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5:: በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ::

———————::1927:: ጥር 16፣ 11ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5:: በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ::

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ::2004:: ገድለ መፈንቅለ መንግስት በኢትዮጵያ 1953 ዓ.ም.:: አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት::

ቴዎድሮስ ገብሬ::2001:: በይነ-ዲስፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ:: አዲስ አበባ::

አበባው ይርጋ::2006:: "የጥምቀት በዓል፣ ምንነቱ፣ ማሕበረ-ባህላዊ አውዶቹና ፋይዳዎቹ::" *Journal of Ethiopian Studies, 39 (1/2)* PP: 151-174.

አዲስ ዘመን ጋዜጣ::1934:: ጥር 16፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 7::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1935::ጥር 16፣ 2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1937::ጥር 16፣ 4ኛ ዓመት፣ ቁጥር 39::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1941::ጥር 14፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 48::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1945::ጥር 16፣ 12ኛ ዓመት፣ ቁጥር ??::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1946::ጥር 15፣ 13ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1947::ጥር 16፣ 14ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1948::ጥር 16፣ 15ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1949::ጥር 13፣ 16ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1951::ጥር 16፣ 18ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1952::ጥር 16፣ 19ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1954::ጥር 16፣ 21ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1955::ጥር 11፣ 22ኛ ዓመት፣ ቁጥር 17::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1956::ጥር 16፣ 23ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1957::ጥር 16፣ 24ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1959::ጥር 16፣ 26ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1960::ጥር 11፣ 27ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1961::ጥር11፣ 28ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1961::ጥር 13፣ 28ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1962::ጥር 12፣ 29ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1963::ጥር 13፣ 30ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1964::ጥር 14፣ 31ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1965::ጥር 16፣ 32ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1966::ጥር 16፣ 33ኛ ዓመት፣ ቁጥር 18::ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

አዕምሮ ጋዜጣ::1926 ዓ.ም:: ጥር 11፣ ቁጥር 33:: ኢትዮጵያ ማተሚያ ድርጅት:: አዲስ አበባ::

እምሩ ዘለቀ (አምባሳደር)::2015:: ጉዞ:: አአዩ ፕሬስ:: አዲስ አበባ::

ዘሪሁን ከበደ::1993:: የአጼ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ:: አአ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

የሮማ ብርሃን ጋዜጣ::1932 ዓ.ም:: የካቲት 3፣ ቁጥር 2:: የኢጣሊያ ምሥራቃዊ አፍሪካ ጠቅላይ ገዢ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር::1992::የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት::አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት::

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና፣ ዛሬና ነገ::1994:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅሳን የዐውደ ርእይ ዐቢይ ኮሚቴ የማስታወቂያና ቅስቀሳ ክፍል የተዘጋጀ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን::2000:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት::

የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ::1949:: ጥር 23፣ ቁጥር 29:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1957:: ጥር 14፣ ቁጥር 43:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

———————::1960:: ጥር 15፣ ቁጥር 68:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

በእደማርያም እጅጉ፡፡2006፡፡ “የምካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ታሪክ፡፡” ያልታተመ፡፡

Alessandro, P. 1997. *The Battle of Valle Giulia: Oral History and Art of Dialogue,* the University of Wisconsin Press.

Allison, R. 1997. <<Personal Experience Narrative>> In Thomas A. Green (Ed), *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art* (PP. 168- 172). California: ABC-CLIO.

Bloor, M. & Wood F. 2006. *Keywords in Qualitative Methods: A Vocabulary of Research Concepts*. London: SAGE Publications.

Burnett, J. 1977. *Usefull Toil*. Harmondsworth: Penguin Press.

Goldstein, K. 1964. *A Guide for Field Workers in Folklore*. Detroit: Gale Research Company.

Hamer, L. 2000. “Oralized History: History Teachers as Oral History Tellers.” *The Oral History Review* 27(2), PP 19-39.

Janesick, J. 2010. *Oral History, for the Qualitative Research, Choreographing the Story*. New York: Guilford Press.

Kothari, R. 2004. *Research Methodology*. New Delhi: New Age International Publisher.

Saltzman, H. 1997. “History, Folk.” In Thomas A. Green (Ed), *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art* (PP. 168- 172). California: ABC-CLIO.

Thompson, P. 1978. *The Voice of the Past: Oral History.* London: OUP.

Vansina, J. 1985. *Oral Tradition as History*. University of Wisconsin Press.

Wudu T. 2006. “The Ethiopian Orthodox Church, The Ethiopian State and The Alexandrian See: Indigenizing the Episcopancy and Forging National Identity, 1926-1991.” Unpublished PhD Dissertation, University of Illinois at Urbaba-Champaign.